መግቢያ……………………………………………………………..2

1. ዓላማ ስትራተጂና ስልት……………………………………………..4

2. ድል ሲባል………………………………………………………….. 5

3. የተሳካ ሽግግር እንዲመጣ……………………………………………6

4. ሰላማዊና የትጥቅ ትግል ስልቶች……………………………………25

5. የሰላማዊ ትግል መልኮችና መርሆዎች……………………………32

6. የሰላማዊ የትግል ስልቶች ተግባራዊነት በኢትዮጵያ………………..39

## *መግቢያ*

*በሃገራችን ኢትዮጵያ የፖለቲካ ስልጣን በሰላማዊ መንገድ የተላለፈበት አጋጣሚ አልታየም:: ስልጣን የያዘው ስልጣኑን የሚለቀው ወይ በተፈቅሮአዊ ሞት ነው ወይ ሌላ ጉልበተኛ መጥቶ በሃይል ሲያስወግደው ነው:: ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር የሚደረግበት የዳበረ ስርዓት ባለመኖሩ ምክንያት አገራችን ለእርስ በርስ ደም መፋሰስ እና ለኢኮኖሚያዊ ድቀት መዳረጓ ደግሞ አሌ የማይባል ነው::*

*ከዚህ የእርስ በርስ ደም መፋሰስና ኢኮኖሚያዊ ድቀት ለመውጣት እንችል ዘንድ የፖለቲካ ስልጣን በህዝብ ምርጫና በሰላማዊ መንገድ እንዲዘዋወር የሚያስችል መደብለ ፓርቲያዊ የፖለቲካ ፉክክርን መሰረት ያደረገ ሕገ-መንግስት በ1987 ላይ ፀድቆ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በየአምስት ዓመቱ ምርጫዎች ሲካሄዱ ቆይታል::*

*እስከአሁን ድረስ ሶስት አገር አቀፍ ምርጫዎች የተካሄዱ ቢሆንም ጠንካራ ፉክክር የታየው 1997 በተካሄደው ምርጫ ላይ ነው::በዚሁ ምርጫ የታየው የፖለቲካ መነቃቃትና በድምፅ መስጠቱ ላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ያሳየው ሰፊ ተሳትፎ ገዢው ፓርቲ ይሁን ተፎካካሪዎች ከጠበቁት በላይ ነበር:: ይህ ሁኔታ ኢህአዴግን ያስደነገጠውና በዚሁም ሳቢያ የመከላከያና የፀጥታ ኃይሎችን በቀጥታ ያሳተፈ ከልክ ያለፈ የኃይል እርምጃ ለመወሰዱ ምክንያት የመሆኑን ያክል ተፎካካሪዎችም ሁኔታውን ያገናዘበ ስልት ማስቀመጥና አመራር መስጠት ተስኖዋቸው ህዝባዊ እንቅስቃሴው ለምትና ለአደጋ እንዲጋለጥ ምክንያት ሆኖአል::*

*ምርጫ 97ን ተከትሎ የተፈጠረው ፖለቲካዊ ቀውስ በሃገራችን ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር ዕጣ ፈንታ ላይ ትልቅ የፖለቲካ ክርክርና ልዩነትን አስከትሏል:: በምርጫው ማግስት እና ከዚያ ቀጥሎ ባሉት ዓመታት ኢህአዴግ እየወሰዳቸው ያሉት እርምጃዎች ግንባሩ በምርጫ ስልጣን ለመልቀቀ ፈቃደኝነቱ የሌለው መሆኑ የሚያሳዩ ስለሆኑ ከእንግዲህ ሰላማዊ ፖለቲካዊ ትግል የሚፈይደው የለም የሚሉ ኃይሎች ተበራክተዋል:: ከዚህ አለፍ ያሉት ደግሞ ትግሉን እንቀጥላለን ከአሁን ወዲያ የምናካሂደው ትግል ግን የትጥቅ ትግልንም የሚጨምር ይሆናል እያሉ ነው::*

*ይህ እንዳለ ሆኖ የፖለቲካ ፓርቲዎችን መስርተው በምርጫ መወዳደርን ጨምሮ ሕገ-መንግስቱ ያረጋገጣቸውን ሁሉም ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በመጠቀም በኢትዮጵያ እየተጣበበ ያለውን ፖለቲካዊ ምህዳር ማስፋትም የፖለቲካ ስልጣን ሽግግር ማምጣትም ይቻላል ብለው የሚያምኑና በዚሁ መሰረት የሚንቀሳቀሱ ወገኖች አሉ::*

*ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል በሃገራችን ብዙም ያልዳበረ በመሆኑ በዚሁ መስክ ጠለቅ ያለ እወቀትና ልምድ የለም:: ከምርጫ 97 የምንማረው ብዙ ጠቃሚ ልምድ እንደሚኖር*

ቢታመንም ከምርጫ 97 ልምድ ብቻ ተነስቶ በኢትዮጵያ በሰላማዊ መንገድ የፖለቲካ ሽግግር የማምጣት ዕድል አብቅቶለታል ለማለት አይቻልም፡፡

በሃገራችን ገለልተኛ ሊባሉ የሚችሉ መንግስታዊ ተቋማት የሉም፡፡ በፓርቲ ፖለቲካና ሙያዊ በሆነው የሲቪል ሰረቪስና የመለዮ ለባሽ ስራ መሃከል ሊኖር የሚገባው ድንበር ከመጥፋቱ ባሻገር እንዲኖርም ኢህአዴግ የሚፈልግ አይመስልም፡፡ ይህ እውነታ ኢህአዴግን በሰላማዊ መንገድ ከስልጣኑ ለማስወገድ የሚነደፈው ስትራቴጂና ስልት ይህንን ያገናዘበ እንዲሆን ግድ ይላል እንጂ ከሰላማዊ መንገድ መወጣትን ግድ አይልም፡፡ የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ እምነት ይህንኑ ነው፡፡ የዚህ ፅሑፍ አላማም በኢትዮጵያ ሰላማዊ ፖለቲካዊ ትግልን ለስኬት ለማብቃት ይቻል ዘንድ መዳሰስ ያለባቸውን ታሳቢዎች ለማመልከት ነው፡፡

## 1. ዓላማ፣ ስትራቴጂና ስልት

የፖለቲካ አላማ የሚባለው በፖለቲካ ትግሉ ተዋናይ የሆኑት ኃይሎች ህዝብ ከመረጠንና ለስልጣን ከበቃን ተግባራዊ እናደርገዋለን የሚሉትን ፕሮግራምና ፖሊሲ ቀምሮ የያዘ ለህዝቡ የቀረበለትንና የተገባለትን ቃል የያዘ የአቋሞችና እምነቶችን ዝርዝር ነው፡፡

የፖለቲካ ስትራቴጂ አላማው ጋር እንዴት እንደሚደረስ የሚያሳይና የሚመልስ የትግሉ ማስተር ፕላን ነው፡፡ትግሉ ከተነሳበት ወቅት ጀምሮ የትግሉ አላማዎች ተሳክተዋል እስከሚባሉበት ጊዜ ድረስ ባለው የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ፣ ለትግሉ ስኬት አስፈላጊ የሆኑት ኃይሎች በቅደም ተከተል ወጥቶላቸው የሚለዩበት፣ በጠቅላላ የትግሉ ምዕራፍ ውስጥ የእነዚህ ኃይሎች ግንባታ እንዴት እንሚከናወን የሚመለስበት፣ በትግሉ ወሳኝ ወቅት የነዚህ ሃይሎች አስላለፍና ስምሪት ምን እንደሚመስል የሚመልስ ፕላን ነው ስትራተጂ ማለት፡፡

የፖለቲካ ስልት የትግሉን እምቅ ኃይለች ወደ ትግሉ እንዲቀላቀሉ የሚያስችላቸውን ከወቅቱ ሁኔታ ጋር የሚስማማ የትግል መልክን እና የአደረጃጀት መልክን እየቀየሰ ትግሉን እንዲቀላቀሉና ተጨባጭ የትግሉ ኃይል ወደ መሆን የሚያሸጋግራቸው የስትራቴጂው ማስፈፀሚያ ዘዴዎችን የያዘ ቀመር ነው፡፡ በአንድ ስትራቴጂካዊ የትግል ምዕራፍ ውስጥ በርካታ ንኡስ ምዕራፎች ሊኖሩ ይችላሉ የፖለቲካ ስልቶች ለንኡስን ምዕራፎች ማሳኪያ የሚመረጡ የትግልና የአደረጃጀት መልኮች ናቸው፡፡በአንድ ንኡስ ምዕራፍም ሳይቀር ከአንድ በላይ ስልቶችን በቅንጅት የመጠቀም ሁኔታ ስለሚኖር አብዛኛው ጊዜ ስለስልቶች ቀመር እንጂ ስለአንድ ስልት ብቻ አይነገርም፡፡ስልቶች ከስትራተጂ የሚለያቸው የትግልና የአደረጃጀት መልክ ጉዳዮች

መሆናቸው፣በስትራተጂክ ምእራፉ እንደሁኔታው ጥቅም ላይ ሊውሉ ወይ ከአገልግሎት ሊወጡ መቻላቸው፣ ሲሆን ስትራተጂ ግን የማይቀየር መሆኑ ነው፡፡ አንዳንድ የትግል መልኮችና አደረጃጀቶች በስትራተጂክ መዕራፉ በጠቅላላ በተከታታይ ጥቅም ላይ ሊዉሉ ይችላሉ፣ ወይ ወጣ ገባ እያሉ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ፣ ይህ ግን ባህርያቸውን የሚወስን አይሆንም፡፡

በአላማ በስትራቴጂና በስልቶች መሃከል ያለው ግንኙነት የተዋረድ ነው፡፡ስትራቴጂን ለመንደፍ የትግሉ አላማ እንደግበአትና መነሻ ይወስዳል፣ ስልቶችን ለመምረጥ እና ለመቀመርም አላማውና ስትራቴጂው እንደግበአት ይወሰዳሉ፡፡ አንድን የተመረጠ የትግል አላማ ለማሳካት በመንገድ ላይ የተገኘን ስትራቴጂ አንስቶ ተግባራዊ አደርጋለሁ ቢሉ ውጤቱ አላማው ዘንድ ላያደርስ ይችላል፡፡ ስልቶቹ እና ስትራቴጂው እንደዚሁ ለየቅል ከሆኑ ብዙ ተለፍቶም የታሰበው ውጤት ላይ ላይደርስ ይችላል፡፡ ከየትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው የሚል መርህ አይሰራም፡፡

በትጥቅ ትግልና በሰላማዊ ትግል አማራጮች መሃከል በሃገራችን ፖለቲከኞች ዙርያ ተነስቶ ያለው ክርክር በስልቶች ዙርያ ያለ ክርክር መሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ከሱ በፊት መጠየቅና መልስ ማግኘት ያለባቸው የፖለቲካ ትግሉ ፕሮግራምና ፖሊሲዎች እና የትግሉ አጠቃላይ ስትራቴጂ ናቸው፡፡ ለእነዚህ መልስ ተይዞ ወደ ስልቶች ቢገባ በትጥቅ ትግልና በሰላማዊ የትግል ስልቶች ዙሪያ ያለውን የሐሳብ ልዩነት ቅጥ ባለው መልኩ ሊከራከሩበትና ሊወያዩበት ያስችላል፡፡ ይህንን ሳያደርጉ በፊት በስልት መረጣ ዙሪያ መከራከርና ልዩነት ማወጅ ቅርንጫፉን ከግንዱ ማስቀደም ይሆናል፡፡

## 2. ድል ሲባል

የትግል መልኩ የትጥቅም ይሁን ሰላማዊ በሁለት ተቀናቃኝ ወገኖች መሃከል በሚደረገው ትግል ውስጥ አንደኛው ወገን አሸነፈ ሌላኛው ተሸነፈ ሊባል የሚቻለው ተሸናፊው የአሸናፊውን ፍላጐት ከማስፈፀም ውጪ ያሉት ሌሎች አማራጮች ሁሉ ዝግ ሲሆኑበት፣ የሚቀረው ብቸኛውና የተሻለው አማራጭ የአሸናፊውን ፍላጐት መቀበልና መፈፀም ሆኖ ሲያገኘው፣ በዚሁም መሰረት የአሸናፊውን ፍላጐት ማስፈፀሙን ሲቀበል ነው(1)፡፡

ተሸናፊው ሽንፈቱን ተቀብሎ የአሸናፊውን ፍላጐት ከማስፈፀም ውጪ ሌላ ማምለጫ አለኝ ብሎ ካመነ አገኘሁ ያለውን አማራጭ ሳይፈትሽ ሽንፈቱን ላይቀበል ይችላል፡፡ አዲሱ አማራጭ ከተሳካለትም የአሸናፊውን ድል ከመሸራረፍ አልፎ

..........

1. Jonathan Schell, The Unconquerable World P17-18

በጠቅላላውም መና ሊያደርገው ይችላል፡፡ ተቀናቃኝ ወገኖች ስትራቴጂ ሲቀይሱ ሌላው ወገን ቢሸነፍም እንኳ ሽንፈቱ እንዳይቀበል ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ምን አማራጭ ማምለጫ መንገዶች ሊኖረው ይችላል ብሎ ማሰብና ለዚሁም አስቀድሞ ማቀድና መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡

ተሸናፊው ወገን የአሸናፊውን ፍላጐት ማስፈፀሙን ሲቀበል ሌላ ማምለጫ አማራጭ መንገድ ስለሌለው ብቻ ሳይሆን የተሻለው አማራጭ ይህ መሆኑንም ማየትና መገንዘብ ይኖርበታል፡፡ ይብዛም ይነስ ተሸናፊው ይበልጥ የሚጠቀመው የአሸናፊውን ፍላጐት ከፈፀመ ብቻ መሆኑን ማየት መቻል ይኖርበታል፡፡ ተሸናፊነቱን ለመቀበሉ እና ለፈቃደኝነቱ በአሸናፊው በኩል ዋጋ የማይሰጠው ከሆነ ተሸናፊው ወደ አጥፍቶ መጥፋት አቅጣጫ ሊገፋ ይችላል፡፡ ስለሆነም ተቀናቃኝ ወገኖች የትግል ስትራቴጂ ሲቀይሱ ሌሎች አማራጮችን ከመዘጋት ባሻገር ለተሸናፊው ወገን ሽንፈትን በፀጋ መቀበል ብቸኛዋና የተሻለችዋ አማራጭ እንድትሆን አድርገው ሊቀይሱዋት ይገባል፡፡

ሁሉም የኢትዮጵያ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ፍላጐታችን የፖለቲካ ስልጣን በነፃ የህዝብ ምርጫ ብቻ የሚያዝበት ሁኔታ በሃገራችን እንዲኖር፣ ይህ ተቋማዊ መልክ ይዞ በማይቀለበስ መደላደል ቆሞ ማየት ነው ይላሉ፡፡ ኢህአዴግ ይህንን እቀበላለሁ በዚሁም ነው በስልጣን ላይ ያለሁት ቢልም ተፎካካሪዎቹ ግን ኢህአዴግ የህዝቡን ውሳኔና ምርጫ አይቀበልም፣ የህዝቡ ውሳኔ ከስልጣን የሚያወርደው መሆኑ ከገመተ ውጤቱን በኃይል መቀልበስ ድረስ እንደሚሄድ ምርጫ 97 ላይ በተግባር አሳይቷል፣ወደፊት በሚኖሩ ምርጫዎች ይህ ሁነታ እንዳይደገምም ሆን ብሎ ፖለቲካዊ ምህዳሩን ለነፃ ውድድርና ነፃ የህዝብ ውሳኔ እንደማይመች እያደረገው ነው ይላሉ፡፡

አሁን ባለው የሃገራችን ሁኔታ ዋና መነጋገሪያ ሆኖ ያለው ጉዳይም እውነት ኢህአዴግን በሰላማዊ ትግል ከስልጣን ማወረድ ይቻላል ወይ? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ ይቻላል አይቻልም ብሎ ለመመለስ እስካሁን ድረስ በተደረጉት ምርጫዎች ኢህአዴግ የህዝቡን ውሳኔ ከመቀበል ውጪ ያሉት ሌሎች መንገዶች ዝግ የሚሆኑበት ሁኔታ ተፈጥሮበት ያውቃል ወይ? ወደፊትስ ይህንን ማድረግ ይቻላል ወይ? የሚለውን ጉዳይ መመርመርና በአጥጋቢ መመለስ ይኖርበታል፡፡

## 3. የተሳካ ሽግግር እንዲመጣ

የተሳካ የፖለቲካ ሽግግር እንዴት ይመጣል የሚለውን መመለስ የሚቻለው እንደየ ሃገሩ ተጨባጭ ሁኔታ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሁኔታ እንኳንስ ከአሜሪካና ከአውሮፓ ይቅርና በበርካታ የአፍሪቃ ሃገራት ዘንድ ካለው ሁኔታም ይለያል፡፡ በሃገራችን የተሳካ ሽግግር ይመጣ ዘንድ ኢትዮጵያ ውስጥ ላለው ትግዳሮት የሚመጥን መልስ ይዞ መምጣት ግድ ይላል፡፡

ኢህአዴግ ገለልተኛ ዳኞች፣ ለሁሉም እኩልና ግልፅ የሆነ የጨዋታ ህግጋት እና ሁሉም ወገኖች የሚወዳደሩበት የተስተካከለ የጨዋታ ሜዳ ባለበት ሁኔታ ከሌሎች ተፎካካሪዎች ጋር ተጫወቶ አሸናፊ ሆኖ ዋንጫውን ቢወስድ የብቃቱ ዋጋና ውጤት ነውና ተሸናፊውም ቢሆን በፀጋና ጨዋ በሆነ ስርዓት ሊቀበለው የሚገባ ይሆናል፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ኢህአዴግ በህዝብ ምርጫ ተሸንፎ እያለ ውጤቱን አልቀበልም ቢል ወይ ለመቀልበስ የሚሞክርበት ሁኔታ ቢፈጠር ግን የህዝቡን ውሳኔ ከመቀበል ውጪ ያሉት ሌሎች መንገዶች ዝግ የሚሆኑበት ሁኔታ መፍጠር ይገባል፡፡ ይህን ለማሳካት የሚቻለው ደግሞ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፡፡

ሀ. የኢትዮጵያ ህዝብ ለኢህአዴግ ድጋፍ መንፈግ ይኖርበታል፡፡ የኢህአዴግ ድጋፍ ከየትኞቹ የሕብረተሰብ ክፍሎች እንደሚመነጭ ከነምክንያቱ መርምሮ እነሱን እንዴት ከኢህአዴግ መንጠቅ ይቻላል? መንጠቅ ካልተቻለስ ገለልተኛ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዴት ይቻላል? የሚሉትን መመለስ ያስፈልጋል፡፡ ይህም ተደርጎ ኢህአዴግ ደጋፊዎች ይኖሩታል እነዚህም ቢሆኑ ግን እጅግ አነስተኛና ደካማ እንዲሆኑ ማድረግ እንዴት ይቻላል? ብሎ መመለስ ያስፈልጋል፡፡

ለ. ለኢትዮጵያ ህዝብ ከኢህአዴግ የተሻለ አማራጭ መገኘትና መቅረብ ይኖርበታል፡፡ አማራጭ ሲባል የህዝቦችዋና የዜጎችዋን ጥቅሞች የሚያስጠብቅና ስጋታቸውን የሚቀርፍ ሚዛናዊ ፕሮግራም ይዞ መገኘትና መቅረብ ማለት ነው፡፡ እነዚህን ኃይሎች ከጫፍ እስከ ጫፍ የሚያስተባብር በዚሁም የተነደፈውን ፕሮግራምና ፖሊሲ ዳር የሚያደርስ በሳል ስትራቴጂና ስልት ይዞ መገኘት ማለት ነው፡፡ ለትግዳሮቱ ይመጥናል ብሎ ህዝብ የሚተማመንበት ኢህአዴግ ዘንድ ካለው የተሻለ አመራር ይዞ መገኘትና መቅረብ ማለትም ነው፡፡

ሐ. የኢትዮጵያ ህዝብ ለዚህኛው አማራጭ ሆኖ ለቀረበለት ኃይል ይሁንታና ድጋፍ መስጠቱን በተፃራሪው ደግሞ ለኢህአዴግ ይሁንታውንና ድጋፉን መንፈጉን በግልፅና በማያሻማ መልኩ በነፃ የህዝቡ ምርጫ መረጋገጥ አለበት፡፡

እንደየ ሃገሩ ተጨባጭ ሁኔታ ስፋትና ጥልቀታቸው ይለያይ እንጂ በማንኛውም ዴሞክራሲ አለ በሚባልበት ሃገር ማንኛውም ተፎካካሪ ኃይል ለስልጣን ይበቃ ዘንድ ከላይ የተጠቀሱት ሶስት ሁኔታዎችን ማሟላትና ማሳካት ይኖርበታል፡፡ ወደ ሃገራችን ሁኔታ ሲመጣ ግን ኢህአዴግ ይሁንታ ትነፍጉትም ስልጣን አልለቅም ይላል ተብሎ ይገመታልና የህዝቡ ይሁንታ ላገኘው ኃይል ስልጣን ከማስረከብ ውጪ ሌላ አማራጭ እንዳይኖረው ለማድረግ የሚከተሉትን ሁኔታዎችንም በተጨማሪ ማሟላትን ግድ ይላል፡፡

መ. መራጩ ህዝብ የምርጫ ካርዱን ኮረጆ ውስጥ አስገብቶ የሚበተን ለውጤቱ ደንታ የሌለው መሆን የለትም:: መራጩ ህዝብ ካርዱን የፅኑ ፍላጐቱና እምነቱ መገለጫ አደርጎ ሊያየው ወደሚችልበት የንቃት ደረጃ እንዲመጣ ማድረግ ይጠይቃል:: ወደዚህኛው የንቃት ደረጃ የመጣ ህዝብ ለምርጫው ውጤት ይጨነቃል ድምፁን ከሰጠ በኋላም ውጤቱን በጉጉት ይጠብቃል:: ከዚህ አልፎም ኢህአዴግ የህዝቡን ውሳኔ አላከብርም ቢል ህዝቡም በበኩሉ ይሁንታ በነፈገው ፓርቲ አልገዛም ለማለት፣ እምቢታውን በሕገ-መንግስቱ በተረጋገጡለት ሰላማዊ ህዝባዊ እርምጃዎች ሁሉ ለመግለፅ ይህንን ቀጣይነትና ፋታ በማይሰጥ መልኩ ለመቀጠል በሚገባ የተዘጋጀና የተደራጀ መሆን ይኖርበታል::

ሰ. ሕገ-መንግስቱ መለዮ ለባሹ እና ሲቪል ሰርቪሱ በፓርቲዎች መሃከል ለስልጣን ከሚደረገው የፖለቲካ ፉክክር ገለልተኛ መሆን እንዳለባቸውና በመንግስታዊ ተቋማትና በገዢ ፓርቲ መሃከል ያለው ድንበር ግልፅ መሆን እንዳለበት ቢደነግግም በአገራችን ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ሲታይ ግን ኢህአዴግ በመንግስትና በፓርቲ መሃከል ሊኖር የሚገባው ድንበር አጥፍቶታል፣ እንዲኖርም የሚፈልግ አይመስልም::

ኢህአዴግ በህዝብ ውሳኔ ላይ ባመፀበት ግን ደግሞ በተደራጀ የህዝብ እምቢታ በተያዘበት ሁኔታ ያደርጋል ተብሎ የሚገመተው የመከላከያና የፀጥታ ኃይሎችን መጠቀም ነው::

በአንድ በኩል በሕገ መንግስቱ መሰረት የሰጠሁትን ውሳኔ ይከበርልኝ የሚል ህዝብ በሌላ በኩል ደግሞ ስልጣን አላስረክብም ባለ ፓርቲ መሃከል ከፍተኛ ፍጥጫ በተፈጠረበት ሁኔታ የመከላከያ እና የፀጥታ ኃይሎች በያንስ ገለልተኛ አቋም እንዲይዙና የገዢው ፓርቲ ወገን ከመሆን እንዲቆጠቡ የሚያደርግ ሁኔታ መፈጠር ይኖርበታል::

ረ. በአሸናፊው ወገን በኩል ለኢህአዴግ አመራር፣ አባላትና ደጋፊዎች የስልጡን ተሸናፊ ክብር ለመስጠት ዝግጁነት መኖሩን የሚያሳዩ ፖሊሲዎች ሊኖሩት ይገባል:: እነዚህንም ቅንነትና ተአማኒነት ባለው መልኩ ይፋዊ ማረጋገጫ ሊሰጥባቸው ይገባል::

በ. አለማቀፉ ማሕበረሰብ ለነፃ ምርጫ መኖርና ለተገኘው ውጤት መከበር ሙሉ ድጋፍ እንዲሰጥ ማስቻል ያስፈልጋል:: ይህ እንዲሆን ለምርጫው በሚደረገው ቅድመ ዝግጅት በቂ ክትትል እንዲኖረው፣ በምርጫው ወቅት በስፋት እንዲታዘብ የሚያስችለው ሁኔታ እንዲኖር፣ ኢህአዴግ በማያሻማ ሁኔታ ይሁንታ አጥቶ አያለ በኃይል ለመቀጠል በሚፈልገበት ሁኔታ ደግሞ አቋሙን በይፋ የሚገልፅበት

ሁኔታ እንዲኖር መስራት ያስፈልጋል:: ከዚህም አልፎ የህዝቡን ውሳኔ ከመቀበል ውጪ ያሉት ሌሎች አማራጮች ሁሉ የሰላምና የመረጋጋት ጠንቆች መሆናቸውን በመሬት ላይ ካለው ሁኔታ መገንዘብ ይኖርበታል::

እነዚህ በኢትዮጵያ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር ፕሮጀክት ስኬት ወይም ክሽፈት የሚወስኑ የአላማና የስትራቴጂ ጥያቄዎች ናቸው፡ እነዚህ አጥጋቢ በሆነ ደረጃ መልስ ተገኘላቸው ማለት በሌላ መልኩ በሃገራችን ለዴሞክራሲ የሚደረገው ትግል የሚመጥነው ስትራቴጂካዊ አመራር አገኘ ማለትም ነው::

እስካሁን ድረስ በዚህች አገር ለፖለቲካዊ ስልጣን በተደረጉት ሰላማዊ ፉክክሮች ለእነዚህ ጥያቄዎች በቂ ምላሽ ይዞ የገባ ተፎካካሪ ድርጅት ወደ ጥምረት አልነበረም:: ለእነዚህ ተግዳረቶች በቂ መልስ ሰጪ ባልቀረበበት ሁኔታ ኢህአዴግን ከስልጣን ማስወገድ አይቻልም፣ እሱም እምቢ እንዳለ ይቀጥላል:: ይህንን ፕሮጀክት ለማሳካት በቂ ጥረት ተደርጎ የማይሰራ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የትጥቅ ትግል አማራጭ ማቀንቀን ቢያንስ ወቅቱ አይደለም:: መጀመሪያ ችግሮቹን ተቋቁሞ ይህንን የቤት ስራ መስራት ይገባል::

ይህንን መከራከሪያ ለማሳየት ነጥቦቹን ይበልጥ ዝርዝር አድርጎ ማየት ያስፈልጋል::

### 3.1 <u>የኢህአዴግ ከህዝብ መነጠል</u>

ኢህአዴግ አለኝ ይል የነበረው የህዝብ ድጋፍ ምን ያህል ተቦርቡሮ እንደቆየ ምርጫ 97 ግልፅ አወጥቶታል:: በኢህአዴግ ላይ ያለው የህዝብ ቁጣና ቅሬታ ምን ያህል ትልቅ እንደሆነ በከተሞች ካገኘው ደካማ የመራጭ ድጋፍ ለመገንዘብ ይቻላል:: እንደ ከተሞቹ ደምቆ ባይነበብም በገጠርም አለ ሲባል የነበረው የአርሶ አደሩ ሙሉ ድጋፍ ምን ያህል እንደተቦረቦረ ተፎካካሪ ድርጅቶች በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ካገኙዋቸው ወንበሮች የሚታይ ነው::

ይህም ሆኖ ኢህአዴግ ደጋፊ የለውም፣ የህዝብ ድጋፉን ተነጥቋል ማለት አይቻልም:: በስልጣን ላይ ለብዙ ጊዜ እና ያለከልካይ የፈለገውን ሲደነግግና ሲፈፅም የቆየ ፓርቲ ነው:: በእነዚህ በስልጣን በቆባቸው ዓመታት የመንግስት ተቋማትን በራሱ መልክና ከራሱ እምነት አኳያ ለሚቋቋም ችሎአል:: በባጀት፣ በቅጥር በሰራተኛ አስተዳደር የመወሰን ስልጣን ያለው ፓርቲ በመሆኑ፣ በመሬት በብድር በኢንቨስትመንት እና የስራ ፈቃድ መስጠት እና በሌሎች ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች ዕደላ ላይ ወሳኔ ሰጪነት በእሱ እጅ ያለ በመሆኑ እነዚህን እንደ ትልቅ ድጋፍ ማስገኛ መሳሪያዎች እየተጠቀመባቸው ይገኛል:: ድጋፍ ሊሰጥ ያልፈለገውም ቢሆን በእነዘህ አገልግሎቶች በኩል ሊደርስበት

የሚችለውን ቁንጠጣ ስለሚያሰጋው በፖለቲካ ፉክክሩ የዳር ተመልካች እንዲሆን ይገደዳል::

ኢህአዴግ የብሄር ጥያቄ በኢትዮጵያ ትልቅ የፖለቲካ ስፍራና እውቅና እንዲኖረው ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል:: ይህንን ጥያቄ ከአጠቃላይ የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ነጥሎ መፍትሄ ለመስጠት እየተከተለው ባለው የተሳሳተ ፖሊሲ ምክንያት አሁንም ጥያቄው መፍትሄ ባያገኝም በዚህ ጥያቄ ዙሪያ በወሰዳቸው አቋሞች ምክንያት ቀላል ያልሆነ ድጋፍ አግኝቶበታል:: በአንዳንድ ተፎካካሪ ፓርቲዎች በኩል በዚህ ጉዳይ ላይ በነበረው ግልፅ ያልሆነ አቋም እና አልፎ አልፎ ይታዩ የነበሩት ግልፅ የጥላቻ ቅስቀሳዎች ቀላል በማይባሉ የሃገራችን ብሄር ብሄረሰቦች ላይ ስጋት መፍጠሩ አልቀረም::ኢህአዴግ ይህንን የተፎካካሪዎቹን ድክመት እና እሱ የፈጠረውን ውዥንብርና ስጋት በማራገብ ለራሱ ድጋፍ ማጠናከሪያ ተጠቅሞበታል::

ምርጫ 97 በፈጠረው ውዥንብርና አፈና ምክንያት በሃገሪቱ ያለው ሁኔታ አዳዲስ ክስተቶችን እያሳየ ነው:: በተፎካካሪዎች ሰፈር መዳከምና መከፋፈል ተከስቷል:: ምንም እንኳ በአወንታ ሊታዩ የሚችሉ የመስከንና የመብሰል ሁኔታዎች ብቅ ብቅ የማለታቸው ሁኔታ ቢታይም የመዳከሙ ሁኔታ የጐላ ነው:: በዚህ ምክንያት ህዝቡም የመቀዝቀዝና በተፎካካሪዎች ላይ የነበረው እምነት የመቀነስ ሁኔታ ይታያል:: ኢህአዴግ በበኩሉ ከምርጫ 97 ማግስት በሕብረተሰቡ ላይ የጣለውን የመደናገጥና የፍርሃት ሁኔታ እንዲቀረፍ የሚያደርግ እርምጃ ከመወሰድ ይልቅ እንዲቀጥል የሚያደርጉ ሕጐችን መደንገግ ነው ይዞ ያለው:: የተፈጠረውን የተፎካካሪዎች መዳከምና በሕብረተሰቡ ያለውን የፍርሃት ድባብ በመጠቀም ደጋፊዎቹን የማብዛትና መዋቅሩን ቤተሰብ ድረስ እንዲዘልቅ እያደረገ ነው (1)::

የኢህአዴግ ደጋፊ ብዙ ላይሆን ይችላል፣ሆኖም ግን የአንድ መንግስትን ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሩ ስር ያደረገ ገዢ ፓርቲ ተደጋፊ መሆኑ ሊጤን ይገባዋል:: አብዛኛው ህዝብ በፍርሃት ዝምታን በመረጠበት፣ አለሁላችሁ የሚልና ዓይኑን የሚሞላለት ጠንካራ አማራጭ ባልቀረበበት ሁኔታ ሜዳው ሁሉ ለኢህአዴግ ሲተው ያ የኢህአዴግ አነስተኛ ደጋፊ ገዝፎ ሊታይ የሚችልበት ሁኔታም ሊፈጥር ይችላል::

ማንኛውም ኢህአዴግን የሚፎካከር ድርጅት ይህንን እውነታ የተገነዘበ ስትራቴጂ መንደፍ ይጠበቅበታል የኢህአዴግ ደጋፊ አነስተኛ ነው ብዙኃኑን ከያዝኩ እሱ የትም አይደርስም ማለት ስህተት ነው:: ከኢህአዴግ ሊነጠቅ የሚችለውን ደጋፊ ለመንጠቅ የሚያስችል፣ ገለልተኛ ማድረግ የሚቻለውን ደግሞ ጥጉን የሚያስይዝ ፖሊሲ ነድፎ

.................

1. ህዳር11/2000 የሕ.ወ.ሓ.ት. ፅ.ቤት ለአባላቱ ያሰራጨው መመርያ

ጥጉን እንዲይዝ በማድረግ መጨረሻ ላይ ከኢህአዴግ ጋር ተለጥፎ የሚዘልቀውን እጅግ አነስተኛና ደካማ እንዲሆን የሚያደርግ ስትራቴጂ ነው መንደፍ ያለበት።

### 3.2 አማራጭ የመገኘቱ ጉዳይ

ኢህአዴግ በስልጣን በቆየባቸው ዓመታት አማራጮቹን ይሞክርና ለውጥ ያመጣ ዘንድ የኢትዮጵያ ህዝብ ሰፊ ዕድል ሰጥቶታል፣ ታግሶታልም። ድርጅቱ ግን እድሉን አልተጠቀመበትም። በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ህዝብ በኢህአዴግ ለውጥ ይመጣል የሚል ተስፋው ተሟጧል ማለት ይቻላል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ለውጥ መፈለጉን ምርጫ 97 ላይ በግልፅ አሳይቷል። ኢህአዴግና አጋሮቹ ዕድሜ ጠገብ መዋቅርና ልምድ፣ ገዢ ፓርቲ መሆን የሚያስገኝላቸውን ጥቅም ይዘው ከረዥም ጊዜ ዝግጅት በኋላ በገቡበት 97 ምርጫ ላይ ምን ያህል እንደተንገዳገዱ በሚገባ አይተውታል።

ይህም ሆኖ ያኔ የታየው የተፎካካሪዎች መሰባሰብ ከዚያ በፊት ከነበረው መሰባሰብ ጋር ሲነፃፀር የተሻለ ቢሆንም ኢህአዴግንና አጋሮቹን በምርጫ ከስልጣን ማውረድ ከሚለው ግብ አንፃር ሲታይ ግን በቂ እንዳልሆነ ምርጫ 97 ራሱ በግልፅ አሳይቷል። ግቡን ለማሳካት 97 ከታየው የበለጠ ጥልቀትና ስፋት ያለው ትብብር መፍጠር ይጠበቅባቸዋል።

የዳበሩና ከፓርቲዎች ፖለቲካ ገለልተኛ የሆኑ መንግስታዊ ተቋማት ባሉባቸው አገራት ልል የሆነ ሕብረት ይዞም በስልጣን ላይ ያለ ፓርቲን ከስልጣን ማስወገድ ይቻላል፣ በምርጫው ስኬት ከተገኘ በኋላ ቀደም ብለው እልባት ያላገኙት ጉዳዮች እልባት ያገኙ ዘንድ ቁጭ ብሎ ለመወያየትና ለመደራደር ፋታ ይገኝ ይሆናል። ከአገራችን የተቋሞች ሁኔታና ካለችበት አካባቢያዊ ሁኔታ አንፃር ሲታይ ለእኛ አገር የተሻለው አካሄድ አህአዴግን ካሰወገዱ በኋላ በሚቋቋመው መንግስት እና በሚከተላቸው ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ዙሪያ መለስተኛ የጋራ መግባባት አስቀድሞ መፍጠር ነው።

የፖለቲከኞች መተባበር በኢትዮጵያ ከሚኖረው የፖለቲካ ስልጣን ሽግግር አንድ ትልቅ እርምጃ ነው።:: የፖለቲከኞች ትብብር ኢትዮጵያውያንን ከጫፍ እስከ ጫፍ ለማስተባበር እጅግ አስፈላጊ መሸጋገሪያ ድልድይም ነው። ወሳኙ እርምጃ የመላ ኢትዮጵያውያን ትብብር በመሆኑ፣ ቀጥሎ መታሰብ ያለበት ትልቁ ጉደይ ህዝቡን እንዴት በዚህ ፖለቲከኞች በፈጠሩት ሕብረት ዙሪያ እናስባስብ፣እናስተባብር፣ የሚለው ነው።

በአንድ ሃገር ያሉ ዜጎች የጋራ ማንነት ይኑራቸው እንጂ ሁሉም አንድ ፍላጐት፣ ጥቅምና ስጋት የላቸውም። እነዚህን ፍላጎቶቻቸውንና ስጋቶቻቸውን መሰረት አድርገው ነው ምርጫቸውን የሚገልፁት። ዞሮ ዞሮ ኢትዮጵያውያን በኢህአዴግና ተፎካካሪዎቹ

በሚፈጥሩት ሕብረት መሃከል ምርጫቸውን የሚሰጡት የትኛው ወገን ይበልጥ ስጋታችንን ይቀርፍልናል፣ ጥቅማችንና ፍላጐታችንን ይጠብቅልናል፣ ከሚለው መለኪያ በመነሳት ነው:: በጥላቻና በቁጣ ወይም በወንዝ ልጅ ስሜት የሚደረግ ውሳኔና ምርጫ አይኖርም ባይባልም ውስጡ ላይ ዘልቀው የሚያገኙት ግን ስጋቱን ማን ይበልጥ ይቀርፋል? ጥቅሙንና ፍላጐቱንስ ማን ያሳካል ተብሎ ይታመናል? ነው::

ኢትዮጵያውያን በአገራችን ደህንነት ነፃነትና ሉአላዊነት ዙሪያ የሚያሳስቡን የጋራ ስጋቶች አሉን:: እኛ ኢትዮጵያውያን በብሄር ብሄረሰብ መብቶቻችን ዙሪያ፣ በሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻችን ዙሪያ፣ በአንድነታችንና እኩልነታችን ዙሪያ እንዲከበሩ የምንጠብቃቸው መብቶችና እሴቶች እንዳሉን ሁሉን እንዳይጓደሉብን የምንሰጋቸው ጥቅሞችም አሉን:: በኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ጉዳዮች ዙሪያም እንዲሁ እውን ይሆኑ የምንላቸው ጥቅሞችና ፍላጐቶች አሉን:: እነዚህን ጥቅሞችና ስጋቶች በሚገባ የተገነዘበና የቀመረ የኢትዮጵያን ህዝቦች ከጫፍ እስከ ጫፍ ሊያነቃንቅ የሚችል አማራጭ ፖሊሲና ፕሮግራም ይዞ መገኘት ይጠበቃል::

የኢህአዴግ ተፎካካሪዎች ሕብረት የፖለቲከኞች ሕብረት ከመሆን አልፎ ለኢትዮጵያ ህዝብ የተሻለ አማራጭ ለመሆን የሚበቃው ይህንን በብቃት ለማከናወን ሲችል ነው::

### 3.3 ይሁንታ የመስጠት/ የመንፈግ ጉዳይ

ኢህአዴግ ከደጋፊዎቹ ተነጥለዋል ወይ? አማራጩ ለህዝበ ቀርቦ ህዝቡስ ደግፎታል ወይ? የሚሉት ጥያቄዎች ከግምት ያለፈ ቁርጥ ያለ መልስ የሚያገኙት በምልአተ ህዝቡ ምርጫ ወቅት ነው:: የኢትዮጵያ ህዝብ ለኢህአዴግ ይሁንታ መንፈጉን በተፃራሪው ለአማራጩ ወገን ይሁንታ መስጠቱን በምርጫ መረጋገጥ አለበት:: ይህ የህዝብ አመለካከትና ውሳኔ ምርጫ 97 ላይ የአዲስ አበባ መራጭ እንዳሳየው በግልፅና ለማድበስበስ በማይቻል መልኩ በህዝበ የምርጫ ካርድ መተላለፍ አለበት::

አዲስ አበባ በምሳሌነት ሲነሳ ኢህአዴግ ለመሸነፉ ማረጋገጫ እንዲሆን እንደ አዲስ አበባው ተፎካካሪው ወገን ዘጠና ከመቶው እና ከዚያ በላይ ማግኘት ግድ ነው ለማለት አይደለም:: ዋናው ጉዳይ ውጤቱ በግልፅና በማያከራክር መልኩ ኢህአዴግ መሸነፉን የሚያሳይ መሆኑ ላይ ነው:: ይህ እውነታ በአብዛኛዎቹ የሃገሪቱ ክልሎች መታየቱ በጣም አስፈላጊ ነው:: ይህ እውን ሲሆን መላ የሃገሪቱ ህዝቦች ኢህአዴግን «ከእንግዲህ በቃ» እንዳሉት ምንም ማስተባበያና መሸፋፈኛ በሌለው መልኩ ለመከላከያና የፀጥታ ተቋማት በግልፅ ይታያቸዋል፣ ለአለምአቀፉ ማሕበረሰብም በግልፅ ይነበባል:: በእንደዚህ ያለ ሁኔታ ኢህአዴግ ድምፅን ለመስረቅ መደበቂያ ያጣና የሚቀረው አማራጭ ወይ ውጤቱን መቀበል ወይም ኃይል መጠቀም ብቻ ይሆናል::

የህዝብ ይሁንታ ያገኘው ወገንም በማያሻማ መልኩ ተለይቶ መውጣት ይኖርበታል ኢህአዴግ ተሸንፎ እያለም ተፎካካሪዎቹ ያልተጣመሩና ከመሃከላቸው ማነው ይበልጡኑ ወንበር ያገኘው? በሚለው ላይ ወደ ውዝግብ ከተገባ፣ በኋላስ መንግስት እንዴት ነው የሚመሰረተው? የሚለውን ለመወሰን ጊዜ የሚጠፋ ከሆነ በመሃል የሚፈጠረውን ውዥንብር ተጠቅሞ ኢህአዴግ ችግር ሊፈጥር ይችላል:: በመሃል ላይ አንጉል የሆነ ሁኔታ ከተፈጠረ በመከላከያና ፀጥታ ኃይሎች እና በአለማቀፍ ማሕበረሰብ ያለመተማመን መንፈስ ሊፈጠር ይችላል:: ኢህአዴግ ይህን ሁኔታ ተጠቅሞ የህዝቡን ምርጫ መና የሚያስቀር እርምጃ ሊወስድ ይችላል::

ኢትዮጵያ ውስጥ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር እና ከምርጫ 97 ልምድም ለመማር እንደሚቻለው የኢትዮጵያ ህዝብ ለኢህአዴግ በማያሻማ መልኩ ይሁንታውን መንፈጉ፣ ለተፎካካሪው በግልፅ ይሁንታ መስጠቱና አሸናፊው ወገን ማን መሆኑ በግልፅና በወቅቱ መታወቁ መሳካት ያለባቸው በጣም አስፈላጊ ሁኔታዎች ናቸው::

ስልጣን ከምርጫ ካርድ ብቻ በሚገኝባቸው ዴሞክራሲያቸው በጠንካራ ተቋማዊ መሰረት ላይ በጣሉ ሃገራት ላይ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር ለማምጣት እስካሁን የተገለፁትን ሟሟላት በቂ ይሆናሉ:: ከእኛ አገር ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ሲታይ ግን እነዚህ ብቻቸውን በቂ አይሆኑም::

ኢህአዴግ የህዝቡ ይሁንታ ተነፍጐት ሲያበቃም ስልጣኑን የህዝብ ይሁንታ ለተሰጠው ወገን አላስከረክብም ይላል ተብሎ ይገመታልና፣ በግልፅና በማያሻማ መልኩ በተሸነፈበት ሁኔታ የህዝበን ውሳኔ ከመቀበል ውጪ ሌላ አማራጭ እንደሌለው፣ ከሁሉም አማራጮቹ ውስጥ የተሻለው አማራጭ እሱ መሆኑን፣ እንዲገነዘብና እንዲቀበል የሚያደርግ ማትግያም አስገዳጅም ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል:: ከዚህ በታች ያሉት በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የግድ መታሰብ ያለባቸው ስትራቴጂካዊ ጉዳዮች ናቸው::

### 3.4 ህዝብ ድምፁን ለማስከበር የተዘጋጀ እና የተደራጀ መሆን አለበት

መራጩ ህዝብ መረጠ ሊባል የሚቻለው የሚያጓጉ አማራጮች ቀርበውለት፣ ከእነሱ መሃል መክሮና ተማክሮ ይበጀኛል ያለውን ሲመርጥና የምርጫውን ውጤት በጉጉትና በከፍተኛ ያገባኛል ባይነት ሲከታተል ነው::

ለመምረጥ ብቁ ከሆነው ዜጋ ምን ያህሉ ተመዘገበ፣ ከተመዘገበውስ ምን ያህሉ ድምፁን ሰጠ የሚሉ ቁጥሮች ጠቃሚ አመልካቾች ናቸው:: ትክክለኛ አመልካችነታቸው የሚመዘነው ግን ህዝቡ በራሱ ፍላጐት ወጥቶ ሲመዘገብና ሲመርጥ ነው:: በራሱ ፍላጐት ይህን ሊያደርግ የሚችለው ደግሞ መምረጥና አለመምረጥ ከወደፊት የራሱና የልጆቹ ዕጣ ፈንታ ጋር ሲያይዘው ነው::

ይህ ከሌለ ምርጫው የኢህድሪ ስርዓትን ጨምሮ የቀደሞቹ ሳሻሊስት ነን ባይ አገሮች ዘንድ ይደረግ እንደነበረው ዓይነት ይሆንና ጉዳዩ የፖለቲካ ለውጥ መኖር አለመኖር መሆኑ ተዘንግቶ ይህን ያህል ፐርሰንት ተመዘገበና መረጠ ዓይነቱ የስታስቲክስ ጨዋታ ብቻ ይሆናል:: በኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር መሰረት በኢትዮጵያ እንዲኖር የሚፈለገው ምርጫ የዚህ ዓይነቱ ለመሆኑ ከሚያዝያ 2000 ምርጫ የተሻለ ማስረጃ የለም::

ኢህአዴግ በከፍተኛ ድምፅ የማሸነፉ እርግጠኛነት አስቀድሞ የታወቀ እና በምርጫ ነው ስልጣናችንን ያስቀጠልነው ለማለት ብቻ የሚካሄድ ስነ ስርዓት እንዲሆን ነው የሚፈለገው:: ህዝቡም የመንግስት አሥራት ማስገባት ያክል ግዴታ ሆኖበት፣ ያሉትን ካላደረግንላቸው አያስቀምጡንም ከሚል የሚሰለፍላቸው፣ስለ ውጤቱ ምንም ደንታ የሌለው ህዝብ እንዲሆን ነው የሚፈልጉት::

የኢህአዴግ ተፎካካሪዎች ሃገራችን ወደ ፊት ከምትሄድበት አቅጣጫ አኳያ ትልቅ ፋይዳ ላለው ምርጫ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል:: ይህንን ለማሳካት ይችሉ ዘንድ መጀመሪያ ራሳቸው ፋይዳ ያለው ስብስብ፣ ፋይዳ ያላቸው ሰዎች እና ፋይዳ ያላቸው አቋሞች ይዘው መገኘትና መቅረብ ይጠበቅባቸዋል:: ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ ህዝቡን ፋይዳ ላለው ምርጫና ትግል ማዘጋጀትና ማብቃት ይኖርባቸዋል::

ምርጫ 97 የኢትዮጵያ ህዝብ ለምርጫ የሚሰጠው ፋይዳ ትልቅ እንደሆነ በግልፅ አሳይቷል:: ገዢው ፓርቲ ያኔ የታየውን የነፃነት መንፈስ አንሰራርቶ እንዳይመለስበት ጥረት አያደረገ ቢገኝም የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ያ መንፈስ መመለሱ አይቀሬ ነው:: ያ መንፈስ እንዲመለስ እና የማይቀለበስ ኃይል ሆኖ ለድል እንዲበቃ ግን መሠራት ያለባቸወ ተጨማሪ ስራዎች ይኖራሉ:: ከነዚያ ውስጥ የሚከተሉትን ዋና ዋና ስራዎች መጠቆም ይቻላል::

**3.4.1 <u>ምልአተ ህዝቡን የማደራጀት ጥያቄ</u>**

የኢትዮጵያ ህዝብ በትዕግስትና ስነ ስርዓት በተላበሰ መልኩ የምርጫ ካርዱን መጠቀም የሚችል መሆኑ በሚገባ አሳይቷል:: ለወደፊትም ይህን ማድረግ እንደሚችል ጥርጥር የለውም::በኢትዮጵያ ሁኔታ ግን ይህ ብቻውን በቂ አይሆንም::ህዝቡ ድምፅ መስጠት ብቻ ሳይሆን ድምፁንም የማስከበር መብትም ግዴታም እንዳለበት ተገንዝቦ ለዚህ የሚሆን ዝግጅትም ሊኖረው ይገባል::ድምፁን ከሰጠ በኋላ ወደየቤቱ እና ወደ የስራ ቦታው የሚበታተን መራጭ መሆን የለበትም::

ኢህአዴግ መሸነፉን ህዝበ ራሱ እያወቀ የህዝቡን ውሳኔ ረግጦ ለመሄድ በሚፈልግበት ጊዜ አይሆንም ብሎ ተቃውሞውን መግለፅ የሚችልበት የራሱ ሃይል ሊኖረው ይገባል:: ድምፁን በስነ ስርዓት መስጠት የሚችል ህዝብ ድምፁ ሲሰረቅበት

ድምፄን አክብሩልኝ ለማለት እና ሲልም ተደማጭነት ሊያገኝ የሚችለው ማስከበርያ መሳሪያው ሲኖረው ነው፡፡ ይህ መሳሪያ ጠበንጃና መድፍ አይደለም፣ ድርጅት ነው፡፡

ፖለቲካ ፓርቲዎች የራሳቸው መዋቅር ይኖራቸዋል፡፡ ይህንን መዋቅራቸውን እስከ ቀበሌ ድረስ ወርዶ አቋሞቻቸውን እንዲያስተጋባላቸው መብቶቻቸውንና ጥቅሞቻቸውን እንዲያስጠብቅላቸው ያደርጋሉ፡፡ ይህ አንድ መስራት ያለበት ትልቅ ስራ ሆኖ እርሱ ብቻውን ግን በቂ አይሆንም፡፡

ህዝብ እንደ ህዝብ የፓርቲ አባል ሊሆን እና በፓርቲ መዋቅር ውስጥ ሊታቀፍ አይችልም፡፡ የፈለገውን እንዲመርጥ እንደተጠየቀውና እንደመረጠው ሁሉ ፍላጐቱንና ምርጫውን እንዲከበርለት ለመጠየቅና ድምፁን ለማስከበር የሚያስችለው አደረጃጀት ነው የሚያስፈልገው፡፡ ይህን ለማሳካት ደግሞ ከመረጠበት ቀበሌ እና ወረዳ የሚጀምር መራጩ ድምፁን ለማስከበር የሚያስችለው አደረጃጀት እንዲኖረው ማድረግ ግድ ይላል፡፡

በሕብረተሰቡ ውስጥ ያሉና ብዙ የቆዩ ሲቪክ አደረጃጀቶችም እንዳሉ ይታወቃል፡፡ እነሱም ቢሆን መራጭ ዜጎችን ያቀፉ እና የተወሰኑ የሕብረተሰብ ክፍሎችን የዜግነት መብት እና ጥቅም ለማስከበር የቆሞ እንደመሆናቸው፣ የዜጎች የመምረጥ መብት ሲረገጥ በዝምታ ያልፉታል ተብሎ ስለማይጠበቅ፣ እንደ አንድ የተደራጀ የህዝብ አካል ሊታሰቡ ይችላሉ፡፡ሌሎች አዳዲስ አደረጃጀቶችም ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡

በአንድ ሃገር ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የመገንባት ስራ የፖለቲካ ፓርቲዎች ስራ ብቻ አይደለም፡፡ በዋናነት የምልአተ ህዝቡ ስራ እንደመሆኑ መጠን ሕብረተሰበ ለመብቱና ለጥቅመ እንዲታገል የሚያስችለው ይበጃል ያለውን አደረጃጀት መስርቶ ለመብቱና ጥቅሙ መቆም መልመድ አለበት፡፡

ከፓርቲዎች ያለፈ ወደ ምልአተ ህዝቡ የዘለቀ አደረጃጀት በማይኖርበት ጊዜ አምባገነን መንግስታት የፖለቲካ መሪዎችን በማሰርና የፓርቲዎችን እንቅስቃሴ በመግታት ብቻ የሚገጥማቸውን ተቃውሞ በቀላሉ ለማፈን ይቻላቸዋል፡፡ ከፓርቲዎች አደረጃጀት በተጨማሪ ሰፊ የህዝብ አደረጃጀት ካለ ግን የተደራጁ ሚልዮኖችን ማፈን አስቸጋሪ ስለሚሆንበት ጥቂት መሪዎችን በማሰር የማይመለስ ይሆንበታል (1)፡፡ እንደዚህ ያለን ህዝብ ደግሞ ገዢዎቹ ይፈሩታል ድምፁንም ያከብሩለታል፡፡ በሚልዮኖች መርጠው ሲያበቁ በተናጠል ከመጮህና ከመታገል ወጥቶ ሚልዮኖች ሆኖ በአንድ ድምፅ ለመናገር እንዲቻል የግድ ሰፊ ህዝባዊ አደረጃጀት መገንባት ይኖርበታል፡፡

ከምርጫ 97 ሊወሰድ የሚገባው ትልቁ ትምህርት ይህ ነው፡፡ የምርጫ እንቅስቃሴው ሚልዮኖችን ለለውጥ ወደ ሚደረገው ህዝባዊ እንቅስቃሴ እንዲቀላቀሉ አድርጓል፡፡ ይህ ምርጫው ከመካሄዱ በፊት በተካሄዱ ሰልፎች እና የምርጫው እለት ለምርጫው

.....................

1. Democracy in the Third World, Robert Pinkney.p.126

በወጣው የህዝብ ተሳትፎ በግልፅ ታይቷል፡፡ ይህንን ግን የሚልዮኖች ተስፋና ምኞት ከዳር ሊያደርስ በሚችል አደረጃጀት ለማቀፍ አልተቻለም፡፡ የፓርቲዎቹ መሪዎች ገደብ ሲጣልባቸውና ሲታሰሩ ይህ ሁሉ አቅም ተበትኖ ነው የቀረው፡፡ ከዚህ አልፎ ለመሄድ የሞከረው ደግሞ ለምት በመጋለጡ እንቅስቃሴው ግለቱን ጠብቆ ለመቀጠል ሳይችል ቀርቷል፡፡

### 3.4.2 <u>ህዝቡን ለሰላማዊ ትግል የማዘጋጀት ጉዳይ</u>

ለህዝብ ውሳኔና ምርጫ አሻፈረኝ ያለን መንግስት መቃወም መብት ነው፡፡ ለህዝብ ውሳኔ አሻፈረኝ ብሎ በሕገ መንግስት ላይ ያመፀን ፓርቲ በሕገ መንግስቱ መሰረት እንቢ አልገዛልህም ብሎ መቃወም በሞራልም በሕግም ተገቢ ተግባር ነው፡፡ ሰላማዊ እስከሆነ ድረስ ይህንን መብት መጠቀም እንደሚቻልም ሕገ-መንግስታችን ይደነግጋል፡፡

አመፅና ጉልበት አፋኞች የሚመርጡት እንጂ ህዝብ የሚመርጠው መንገድ አይደለም፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ይህንን አመፅ መቃወም የሚገባው በአመፅ ሳይሆን በሰላማዊ መንገድ ነው፡፡ ስልጣን በእጁ የያዘን እና ኃይል ለመጠቀም የቆረጠን መንግስት በጉልበት መሞከር ሊደረግና ሊታሰብ አይገባውም፡፡ አመፀኛ መንግስትን ማሸነፍ የሚቻለው በጥንካሬው በኩል ገብተው ሳይሆን በድክመቱ በኩል ገብቶ መሆን ይኖርበታል፡፡ በዚህ መሰረት ህዝቡ የድምፄ ይከበር ትግሉን ማካሄድ ያለበት ቀጣይነት ባለው ሰላማዊ የህዝብ እምቢታ እና እርምጃ ነው፡፡ የሰላማዊ ህዝባዊ እርምጃና እምቢታ መልኮች ብዙ ናቸው፣ እነሱን ወደ ኋላ ላይ እንመለከታቸዋለን፡፡የትጥቅ ትግል የራሱ ሰራዊትና መሳሪያዎች ያሉት ስልት እንደሆነ ሁሉ ሰላማዊ ትግልም የራሱ መዋግያ ሙያና ትጥቆች ያሉት ስልት መሆኑ ሊጤን ይገባዋል(1) ፡፡ አፋኝ አገዛዝን ከማስወገድ አኳያ አንዱ ከሌላው አያንስም፣ አንዱ ከሌላው አይቀልም፡፡ በሃገራችን መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች የተረጋገጡበት ዴሞክራሲ ይኖር ዘንድ ሰላማዊ የትግል ስልቱን አጥብቆ የያዘ እና አጠቃቀሙን በሚገባ የሚያውቅበት «ሰራዊት» መገንባት ያስፈልጋል፡፡

ድምፄን ይከበርልኝ ያለ፣ በሚልዮኖች የሚቆጠር የተደራጀ ዜጋን ይዞ፣ በሰላማዊ የትግል ስልት ኢህአዴግን ማሸነፍ ይቻላል ብሎ በዚሁ አቅጣጫ ተገቢው ስራ ከተሰራ ምርጫውን መቀልበስ ለኢህአዴግ እጅግ ከባድ ውሳኔ እንዲሆንበት ያደርገዋል፡፡ ህዝቡ ለዚሁ ዓይነት ሁኔታ ካልተደራጀና ካልተዘጋጀ ግን ውሳኔው ቀላል ይሆንለታል፡፡

.........................

*1.* The politics of Nonviolent Action, Gene Sharp p.110

ውሳኔው እጅግ ከባድ እንዲሆንበት ደግሞ ከካርዶቹ በስተጀርባ የተደራጀ እና ድምፁን ለማስከበር የተዘጋጀ ህዝብ መኖሩን እንዲያውቅ ማድረግ ያስፈልጋል።

**3.5 የሲቪል ሰርቪሱ፣ የመከላከያ እና የፀጥታ ኃይሎች ገለልተኝነት ማረጋገጥ**

ሕገ መንግስታችን የዳኝነት ስርዓቱ ከሕግ አስፈፃሚው ተፅእኖ ነፃ ሆኖ ሕጉን እንደሚተረጉም ይደነግጋል። ሕግ አስፈፃማው አካልም ቢሆን ሕዝብ መርጦ ስልጣኑን ለሰጠው የየትኛውም ፓርቲ ፖሊሲዎች ማስፈፀም ግዴታ ይኖረዋል እንጂ የአንድን ፓርቲ ፖሊሲዎች ብቻ ካልሆነ የሌላ አልቀበልም የማለት ስልጣን የለውም። ለዚህም ነው የሲቪል ሰርቪሱ እና የመለዮ ለባሹ ተቋማት ከፓርቲ አደረጃጀት ነፃ ሆነው ራሳቸውን የቻሉ ቀዋሚ ተቋማት ሆነው የሚደራጁት። እነዚህ ለሃገሪቱ እና ለዜጎቿ በጠቅላላ ያለአድልዎ አገልግሎትና ጥበቃ የሚያደርጉ ከሃገሪቷ ዜጎች በሚሰበሰብ ግብር የሚተዳደሩ ተቋማት እንደመሆናቸው መጠን አንድን ኢትዮጵያዊ/ት በፖለቲካ አቋም፣ በሃይማኖት በቀለም እና በብሄር/ዘር ምክንያት ከሌላው/ዋ ወንድም እና እህቱ ለይተው ሊያዩ አይገባቸውም።

ሕገ መንግስቱ ይህን ቢደነግግም ኢህአዴግ በተግባር እየፈፀመ ያለው ከዚህ የተለየ ነው።

**3.5.1 ሲቪል ሰርቪሱ ጋር ያለው ሁኔታ፡-**

ኢህአዴግ ሲቪል ሰርቪሱን ለእሱና ለእርሱ እምነቶችና አቋሞች ብቻ እንዲያገለግል ሆኖ እያቋቋመውና እያጠመቀው ነው። በመንግስት መስሪያ ቤቶች ለመቀጠር እድገት ለማግኘትም ይሁን የከፍተኛ ትምህርት እድል ተጠቃሚ ለመሆን ኢትዮጵያዊ መሆንና የሙያ መስፈርቱን ማሟላት ብቻ አይበቃም፤ የኢህአዴግ አባል መሆን፣ ቢያንስ ደግሞ የኢህአዴግ ደጋፊ መሆንን ግድ ይላል።

የመንግስት ተቀጣሪ ሆኖ የኢህአዴግ አባል ወይም ደጋፊ ሳይሆኑ እንደዜጋና እንደ ሙያተኛ የገዛ ሃገርን እና ወገንን እያገለገሉ በመንግስት ሥራ መዝለቅ እጅግ አስቸጋሪ እየሆነ ነው። እንደዚህ ያለ ዜጋ በአባላት ግምገማ እየተገፋና እየተገለለ ይሄዳል የፓርቲያችሁ አባል አልሆንም ብሎ ድርቅ ካለ ደግሞ የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በቀር መወገዱ አይቀሬ ነውና የኢህአዴግ አባል ያልሆነ የስራ ዋስትና የለውም ። የኢህአዴግ ፓርቲ አባላት ያልሆኑትን ይቅርና አባላቱም የሥራ ዋስትና የላቸውም፣ በግምገማ ሽፋን በማሃከላቸው በሚደረገው የጥሎ ማለፍ ትንቅንቅ ሂደት በአንድ ወቅት ጠንካራ እና ለኢህአዴግ መስመሮች ታማኝ ተብሎ ይወደስ የነበረ ሰው ቀዝቅዟል ተሸክሏል ተብሎ ይገፈተራል።

በእነዚህ ምክንያቶች ሲቪል ሰርቪሱ እርጋታ የለውም፣ በአንድ በኩል የገቡት በሌላ በኩል የሚፈሱበት ቀዳዳ በርሜል ነው:: የተጀመረን ስራና አሰራር መጨረስና ለውጤት ማድረስ ይቸገራል:: ዜጎች ስራ አለን ብለው በስክነት የሚሰሩበት፣ የሙያ ደረጃ አሻሽየ እና ልምድ አካብቼ አድግበታለሁ ብለው ተስፋ የሚጥሉበት እና የረጅም ጊዜ እይታ ይዞ የሚኬድበት ስራ መሆኑ ቀርቷል:: አንድ ቀን መገፍተሬ ላይቀር እስከዚያ ድረስ የሚነጠቅ ካለ ነጣጥቄ ኪሴን ልሙላ የሚል መንፈስ የሰፈነበት፣በርካታ ነጥቆ በረሮች የተሰገሰጉበት ቤት እየሆነ ነው:: ለዚህ ነው በሚገባ የታሰበባቸው እና በተደራጁ ቡድኖች የሚፈፀሙ ከማፍያ ስራ ያላነሱ የዝርፍያ ስራዎች እየሰማን ያለነው:: እነዚህን ሙስና ይሉዋቸዋል:: በዚህ መልኩ የተደራጀ ሲቪል ሰርቪስ ሃገርን ይቅርና ኢህአዴግንም አልጠቀመውም::

ኢህአዴግ ሲቪል ሰርቪሱን በምርጫ ወቅት በግል መሳሪያነት ሊጠቀምበት ይችላል:: ለዚህ ዝግጅት በሚመስል መልኩ ሚያዝያ 2000 በተካሄደው ምርጫ ላይ የወረዳ እና የቀበሌ መስተዳድሮችን አስፍቶ ሙሉ በሙሉ በራሱ አባላት እንዲያዝ አድርጎታል:: ይህ ሁኔታ በሚቀጥሉት ምርጫዎች ላይ የምርጫ አስፈፃሚ አካላትን ሙሉ በሙሉ በራሱ አባላት እንዲያዋቅረው፣ ይህንን ተጠቅሞም የምርጫውን ውጤት ለሱ በሚመቸው እንዲጫወትበት ያስችለዋል:: ይህ እንዳይሆን ከላይ እንደተገለፀው ህዝቡ ድምፁን ለማስከበር እንዲችል በሚገባ የተደራጀ እና የተዘጋጀ መሆን ይኖርበታል::ከዚህ በተጨማሪ ከአለም አቀፍ ተቋማትና ከሌሎች ገለልተኛ ከሚባሉ ተቋማት የተውጣጣ ጠንካራ የምርጫ ታዛቢዎች መዋቅር እስከዝቅተኛዋ የምርጫ ነጥብ ድረስ እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል::

ከሲቪል ሰርቪሱ ሚና ቀጥሎ መታየት ያለበት ጉዳይ የፀጥታ እና የመከላከያ ኃይሎች ሚና ነው::

### 3.5.2 የመከላከያና ፀጥታ ኃይሎች ሁኔታ:-

ሕገ መንግስቱ የሃገር መከላከያ ሰራዊታችን ተልእኮ የሃገርን ዳር ድንበርና ሉአላዊነት ማስከበር መሆኑን ደንግጓል:: በሃገር ውስጥ ፀጥታዊ ስራዎች መሳተፍ ግድ የሚሆንበት ሁኔታ እንዳለ በሕገመንግሰቱ የተመለከተ ቢሆንም፣ ተግባሩን ከፖለቲከ ድርጅቶች ወገናዊነት ነፃ በሆነ አኳኋን ማከናወን እነዳለበትና በማናቸውም ጊዜ ተገዢነቱ ለህገመንግስቱ መሆኑን ተደንግጓል::

ስልጣን ከህዝባዊ ምርጫ ብቻ እንደሚገኝ፣ በህዝባዊ ምርጫ ስልጣኑን የያዘው ፓርቲ መሪ መስተዳድሩን እንደመምራቱ ሁሉ የሰራዊቱም ጠቅላይ አዛዥ እንደሚሆን ሕገ መንግስቱ ይደነግጋል:: ይህ የሚሆነው ለማንኛውም በምርጫ ስልጣን ለያዘ ፓርቲ እና ያ ፓርቲ መስተዳድሩን እንዲመራ ለመረጠው መሪ እንጂ ለአንድ ፓርቲ እና ለዚያ አንድ ፓርቲ መሪ ብቻ አይደለም::

ኢህአዴግ በሃገሪቱ ካሉት ሕጋዊ እወቅና ካላቸው ፓርቲዎች ውስጥ አንዱ ነው። እንደማንኛውም ፓርቲ ለህዝበ የራሱን አማራጭ አቅርቦ ሌሎቹም እንደርሱ የራሳቸውን አማራጭ አቅርበው እና ሁሉም እኩል እድል አግኝተው በሚካሄደው ውድድር አሸናፊወ እንደማለይ ሕገ መንግስቱ ይደነግጋል።

ተወዳድሮ እና በልጦ በመገኘት ለስልጣን መብቃት ፓለቲከዊ ፓርቲዎች ራሳቸው ብቻ የሚወጡት ተግዳሮት መሆኑ ቢታወቅም ገዢ ፓርቲዎች ይህንን የራሳቸው እና የራሳቸው ብቻ የሆነውን ተግዳሮት በራሳቸው ብቃት ማሳካት ሲያቅታቸው የመከላከያ ሃይሉ የእነሱ ወገን ሆኖ ሌላኛውን ወገኑን እንዲያጠቃ እና የእነሱን የሕዝብ ላይ አመፅ መሳሪያ እንዲሆን ያደርጋሉ። የሃገር ውስጥ ፀጥታ መደፍረስ እና የእርስ በርስ ጦርነት የሚከሰተውም እንደዚህ ባለ የፖለቲካ ሁኔታ ነው።

በስልጣን ላይ ያሉ ፖለቲከኞች ከሌሎች ያገር ልጅ ፖለቲከኛ ወገኖቻቸው ጋራ ያላቸውን የፖለቲካ ልዩነት በፖለቲካዊና ሰላማዊ መንገድ ማስተናገድ እና መፍታት ስልጣናቸውን ሊያሳጣቸው ወይም ሊሸራርፍባቸው መሆኑን ሲገነዘቡ ሆን ብሎ የፖለቲካ ልዩነቱ የፀጥታ ችግር ወደ መሆን ደረጃ እንዲሸጋገር በማድረግ የገዛ ራሳቸወን ተግዳሮት የመከላከያ ሃይሉ ተግዳሮት ወደ መሆን ያሸጋግሩታል። ስልጣናቸውን ህዝቡ ለመረጠው ወገን የማስረከቡ «መስዋእትነት» ለመከፈል ወኔያቸው በከዳቸው ቁጥር የመከላከያ ሰራዊቱ አባላት ያለ ግዳጃቸው በሆነ ጉዳይ ውስጥ ገብተው ህይወታቸውን እንዲያሳልፉላቸው ያደርጋሉ።

በዚህ መልኩ የሃገር መከላከያ ሰራዊቱ ዋና ግዳጁ ከሆነው የሃገርን ሉአላዊነትና ዳር ድንበር ከማስከበር ውጪ የሃገርን ፀጥታ ማስከበርና «ፀረ አብዮተኞች» «ፀረ ሰላም» «ፀረ ልማት» «ነውጠኞች» «አሸባሪዎች» ወዘተ. የሚሉ መጠርያዎች የተለጠፉባቸውን ተቃዋሚዎች የማሳደድ ተጨማሪ ግዳጅ ይጨመርበታል።

ይህ በህገ-መንግስቱ ውስጥ ከሰፈረው ግዳጅ ውጪ የሆነው ለመከላከያ ሰራዊቱ የማደረብለት ተጨማሪ ግዳጅ የፖለቲካ መሪዎቹ ስልጣንን በሰላማዊ መንገድ ማስረከብ የምትጠይቀዋን መስዋእትነት ሰራዊቱ በህይወቱ እንዲከፍልላቸው ከመጠየቃቸው ባሻገር ሌሎች መዘዞችም ያሉበት ነው።

መከላከያ ሰራዊቱ በዋናው ግዳጅ ላይ እንዳያተኩርና ሃይሉን በዚሁ ተጨማሪ ግዳጅ ላይ እንዲበትን ያደርጋል። መንከራተቱ እንዲበዛበት ከማድረጉ በሻገር የመከላከያ ሃይሉ መሆን ከሚገባው በላይ ይበዛ እና ለዚሁ የሚመደበው ያገር ሃብት አገሪቱ ከምትሸከመው በላይ እንዲሆንባት ያደርጋል።

ሰራዊቱ የሃገሪቱ እና የመላ ዜጎቿ የጋራ ጥቅም አስጠባቂና አለኝታ መሆኑ ይቀርና በሃገር ውስጥ ፖለቲካ በወገንተኛነት እንዲሰለፍ ይገደዳል። በዚሁም ምክንያት ገዢውን ፓርቲ የማይደግፉት የሕብረተሰብ ክፍሎች ገሸሽ እንዲሉት ይደረጋል። ውሎ አድሮም

ይህ በሕብረተሰበ ያለው ሁኔታ ወደ ሰራዊቱ ይዘልቅና በሰራዊቱ አባላት መካከል ያልተፈለገ ልዩነትና አለመተማመን እስከ መፍጠር ይደርሳል፡፡ የሃገሪቱን ዜጎች የአለኝታነት ክብርና ሞገስ ያጣ ሰራዊት ውስጣዊ አንድነቱ የላላ ከመሆኑ ባሻገር የሃገር ሉአላዊነትና ዳር ድንበር አደጋ ላይ በሚወድቅበት ጊዜም ሁሉም ዜጎች የማይደርሱለት ይሆንና እርሱ ራሱም ዋናው ግዳጁም አደጋ ላይ ይወድቃሉ፡፡ ለሕዝብ ድምፅ የማይገዙ መሪዎች ሰራዊቱን እንወድሃለን ቢሉትም በህዝብ ድምፅ ላይ እስካመፁ ድረስ ውለው አድረው ለሰራዊቱም ጠንቅ መሆናቸው አይቀሬ ነው፡፡

ገዢው ፓርቲ በተቀያየረ ቁጥር የማይቀየር ሰራዊት ይኖር ዘንድ የሃገር መከላከያ ሰራዊት ተገዢነቱ በሕገ መንግስቱ መሰረት ህዝቡ ለመረጠው ፓርቲ የመሆኑ ጉዳይ በጣም ትልቅ ፋይዳ ያለው ጉዳይ መሆኑ ግንዛቤ ሊያገኝ ይገባል፡፡ተወዳድሮ በልጦ መገኘ ት ኢህአዴግ ራሱ የሚወጣው ተግዳሮት እንጂ መለዮ ለባሹ የሚወጣለት ተግዳሮት ሊሆን አይገባም፡፡ ስራዊቱም ይህንን እንዲገነዘብ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ኢህአዴግ የህዝቡን ይሁንታ ባጣበት ጊዜ ህዝቡ ድምፁን ለማስከበር በሚገባ የተዘጋጀ እና የተደራጀ መሆን እንዳለበት ከፍ ብሎ ተመልክቷል፡፡ ይህ ሲሆን ኢህአዴግ ስልጣን ላለማስረከብ ካቅማማ የሚጠብቀው ተከታታይነት ያለው የህዝብ እምቢታና ሰላማዊ ህዝባዊ እርምጃ መሆኑን በግልፅ ይታየዋል፡፡ ይህ ሆኖም እምቢ አላስረክብም ካለ የሚኖረው ብቸኛ አማራጭ የመከላከያ እና የፀጥታ ኃይሎችን በስመ ፀጥታ እና ሕግ ማስከበር ህዝባዊ እምቢታውን በኃይል እንዲመቱ ማድረግ ነው፡፡ ይህ እንደይሳካለት ተፎካካሪው ወገን የመከላከያ ኃይሉ ለሕገ-መንግስታዊ ግዳጁ ብቻ እንዲቆም የሚያደርግ በእንደዚህ ያለ ወሳኝ ወቅት ኢህአዴግ እንዲያደርግ የሚጠይቀውን የጭፍለቃ ስራ ውስጥ እንዳይሰማራ እና ገለልተኝነቱን እንዲጠብቅ የሚያደርግ የፖለቲካ ስራ መስራት ይኖርበታል፡፡

ይህ ፖለቲካዊ ስራ በሰራዊቱ መዋቅር ውስጥ ሰርጎ በመግባት የሚደረግ የድርጅት ስራ እና ሴራ አይደለም፡፡ ሰራዊቱ የሕብረተሰበ አካል በመሆኑ ተፎካካሪዎቹ ለሕብረተሰቡ የሚያቀርቡት አማራጭ ለሰራዊቱም በመገናኛ ብዘሀን በኩል እንደሚደርስ ይጠበቃል፡፡ ተፎካካሪዎች የሃገሪቱ ነፃነት፣ ሉአላዊነትና ጥቅሞችን ከማሰጠበቅ አኳያ፤የብሄራዊ ድህንነት ስጋቶችን ከመቅረፍ አኳያ፤የመከላከያና ፀጥታ ሃይሎቻችን ደህንነትና ዝግጁነት ከማረጋገጥ አኳያ፤ ወዘተ የራሳቸውን የፖሊሰ አማራጮችን መቅረፅ ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህን ኢህአዴግ ከሚከተለው መንገድ ጋር በማነፃፀር ለሃገሪቱም ሆነ ለመከላከያ ተቋሙ እንዴት የተሻሉ እንደሆኑ በሚገባ ማሳየት ይኖርባቸዋል፡፡ በዚሁ አቅጣጫ በብቃት እና በቂ ጊዜ ሰጥተው ከሰሩ በወሳኙ ወቅት ከሰራዊቱ የሚፈለገው የገለልተኝነት አቋም ማግኘት ይቻላል፡፡

ይህ ሲሆን ግን በምንም መልኩ ተፎካካሪው ሊያደርጋቸው የማይገባ ሁለት ነገሮች አሉ:: አንድ የመከላከያ ኃይሉን ለአመፅ ማንሳሳት የለበትም፣ ሁለት ተፎካካሪው ራሱ የሃይልና የአመፅ እርምጃ መውሰድ የለበትም፣ የሃይል እርምጃ በእርሱ ላይ ቢቃጣበት እንኳን የአፀፋ መልስ መስጠትን መከጀል የለበትም::

አካባቢያችን ያልረገቡ የፀጥታ ውጥረቶች ያሉበት አካባቢ እንደመሆኑ፣ ከጐረበት ሃገራት ጋር ማሳረጊያ ያልተበጀለት ግጭት ውስጥ ያለን እንደመሆናችን መጠን የመከላከያ ኃይላችን ህልውና መናጋት የለበትም:: ይህ ተቋም ሕገ መንግስቱ ለሰጠው ተልእኮ ብቻ በታማኝነት እንዲቆም መታገልና መጠየቅ ተገቢ ሆኖ በምንም መልኩ ግን ይህ ተቋም እንዲናጋ መፍቀድ የለብንም:: ኢህአዴግ ሕገ መንግስቱ ካስቀመጠለት ግዳጅ ውጪ ሊጠቀምበት ቢፈልግም እንኳ ተቃዋሚዎች መርህን ተከትለው ይቃወሙታል እንጂ የኢህአዴግን መርህ የለሽ ተግባር በሌላ መርህ የለሽ አፀፋ ሊመክቱ አይገባም::

ኢህአዴግ በህዝባዊ እምቢታው ላይ የመከላከያ እና የፀጥታ ሃይሎችን ለመጠቀም ቢፈልግም እንኳ ሰላማዊ እና ሕጋዊ በሆነ የህዝብ እምቢታ ላይ ግባና ደብድብ ብሎ ትእዛዝ ሊሰጥ መቻገሩ አይቀርም:: ይህንን አልፎ ትእዛዝ ቢሰጥም እንኳ የመከላከያ እና የፀጥታ ኃይሎች ምንም ጥፋት ባልሰራ ህዝብ ላይ የተሰጣቸውን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ ሊቸገሩ ይችላሉ:: በእንደዚህ ያለ ሁኔታ ተፎካካሪው ወገን የስልት ስህተት ፈፅሞ የኃይልና የአመፅ እርምጃ እንዳይወሰድ በንቃት ሊጠብቅ ይገባዋል::እርሱ ሊጀምር ይቅርና ህዝቡን ወደዚህ እርምጃ የሚገፋፋ እርምጃ በኢህአዴግ በኩል ቢወስድ እንኳን ከህዝቡ ወገን አንዳች አፀፋዊ እርምጃ መወሰድ የለበትም:: ይህንን የሚገፋፉ ሴረኞች እንኳን ቢከሰቱ ህዝቡ ሊቆጣጠራቸው የሚያስችል ዝግጅት ሊኖረው ይገባል:: ስልጣኑ ይቀራል እንጂ የአመፅ እርምጃ ፈፅሞ መወሰድ የለበትም፣ እንደዚህ ያለ እርምጃ ፀጥታ ደፍርሷል ብሎ የመከላከያ እና የፀጥታ ሃይሎችን አሰማርቶ እምቢታውን ሊያገግም በማይችል መልኩ እንዲመታው እድል ይሰጠዋል:: ይህ ከሚሆን የህዝቡን ሃይል ከጥቃት አትርፎ ሌላ ቀን መጠበቅ ይሻላል:: ተፎካካሪው ወገን የሚገነባው ሃይል በመንፈስ ፅናቱና በአደረጃጀቱ ይህንን ፈተና ማለፍ የሚችል መሆን ይኖርበታል::

### 3.6 ለኢህአዴግ የስልጡን ተሸናፊ ክብር ስለመስጠት

በኢትዮጵያ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግርን መሳካት ራሱን የቻለ ትልቅ የታሪክ ምዕራፍ ነው:: የዚህ ፕሮጀክት መሳካት በደም መፋሰስ ለታጀበው የኢትዮጵያ የስልጣን ሽግግር ታሪክ መቋጫ የማግኘቱ ትልቅ ጅምር መሆኑ ግንዛቤ ሊያገኝ ይገባል::

ኢህአዴግ በስልጣን በቆየባቸው ዓመታት ብዙ ስህተት መስራቱ የማይካድ ቢሆንም ስልጣንን በሰላማዊ መንገድ እና በምርጫ ካርድ ውጤት ብቻ መገኘት እንዳለበት ተቀብሎ ለአሸናፊው ወገን ለማስረከብ ፈቃደኛ ሆኖ መገኘቱ ደግሞ አንድ ትልቅ

አወንታዊ እርምጃ ነው። ይህን ተግባሩን የምርጫ ውጤቱን ባይቀበልስ ምን ሊመጣ ይችላል ከሚለው ጋር ማነፃፀር ያስፈልጋል።

ጦርነት ከሚያስከትለው የእርስ በርስ መገዳደልና መወጫ የለሽ የድህነት አዙሪት ለመውጣት እስካሰቻለ ድረስ፣ ኢህአዴግ ሽንፈቱን ተቀብሎ ለአሸናፊው ወገን ስልጣን ማስተለለፍ ፈቃደኛ እስከሆነ ድረስ፣ ለዚህ ስራው ዋጋ ይሆነው ዘንድ ኢህአዴግን በዘንባባ ዝንጣፊ መሸኘቱ ከባድ ዳገት ሊሆን አይገባም።

እምቢ ያለ ውሎ አድሮ መሸነፉ እና ለውርደት መዳረጉ ባይቀርም እስከዚያ ድረስ ሃገር የምትከፍለው ዋጋ ግን ከባድ መሆኑ አይቀሬ ነው። ይህ እውነት ስለመሆኑ ያለፉት የአርባ ዓመታት የኢትዮጵያ ታሪክ ራሱ ይናገራል። ያለፈውን ታሪካችንን ከመደጋገም ለሚያስቀረን መንገድ ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ ካልሆንን ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር ብዙ ፈተናዎች ሊደቀኑበት እንደሚችሉ መገንዘብ ይኖርብናል።

ስልጣንን በሰላማዊ መንገድ ለማስተላለፍ ብንፈልግም እንኳ አንዴ ከለቀቅን በኋላ እየተከታተሉ ሊያጠፉን ይችላሉ የሚል ስጋት እንደሚኖር መገመት ይቻላል። ይህ ስሜትና ስጋት ምርጫ 97 ላይ በተለያየ መልኩ ብቅ እንዳለም ለጤን ይገባዋል። የኢህአዴግ ተፎካካሪዎች ይህን ስጋት መቅረፍ የሚያስችል ሰፊ የፖለቲከ ስራ መስራት ይጠበቅባቸዋል። ከዚህ አልፎም በኢህአዴግ መሪዎች፣ አባላት እና ደጋፊዎች ሊኖር የሚችለውን ስጋትም የሚያስወግድ እርምጃ መውሰድ ይጠበቅባቸዋል።

ኢህአዴግ ቢሸነፍም እንደ ተፎካካሪ ፓርቲ እንዲቀጥል የሚያስችል ዋስትና ለመሪዎቹ፣ ለአባላቱና ለደጋፊዎቹ ሊሰጣቸው ይገባል። ዝርዝሩ በውይይትና በጋራ ስምምነት ተመስርቶ ሊሰራ ይችላል፣ መርሁ ግን ከብቀላ በፀዳ መንፈስ ኢህአዴግና መሪዎቹ ነፃነታቸው ተጠብቆ በሃገሪቱ ፖለቲካ ተዋናይ ሆነው እንዲቀጥሉ የሚያስችል ዋስትና የመስጠት ጉዳይ ይሆናል።

እንደዚህ ያለ ዋስትና ገዢው ፓርቲ የዚህን ምርጫ ውጤት ከተቀበልኩ ይህ ችግር ሊመጣብኝ ይችላል ከሚል ስጋት የአጥፍቶ ጠፊ ስልት እንዳይመርጥ በቂ ድጋፍና ማትግያ ይሆነዋል።

### 3.7 ለነፃ ምርጫ የአለም አቀፍ ድጋፍ ስለመሻት

የአለም አቀፍ ማሕበረሰብን ድጋፍ ስለመሻት እና ስለማግኘት ስንነጋገር መታሰብ ያለባቸው ነጥቦች አሉ።

ኢህአዴግ ምርጫ 97ን ተከትሎ በወሰዳቸው እርምጃዎች አለም አቀፉ ማሕበረሰብ ተከፍቷል። የኢህአዴግ አገዛዝ መሰረቱ ደካማና ጠባብ እንደሆነ፣ አሁን ይዞት እየሄደ ያለው አቅጣጫ ዘለቄታ የሌለው እና የኢትዮጵያን ፀጥታ ሊያናጋ የሚችል መሆኑ የመገንዘብና በዚሁም የመስጋት ሁኔታ አለ። የኢህአዴግ መንግስት ይዞት ያለ

አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚባለው ቀመር በተግባር ፀረ- ዴሞክራሲ መሆኑን አለማቀፉ ማሕበረሰብ ይበልጥ እየተገነዘበ የመጣበት ሁኔታም አለ፡፡

የኢህአዴግ የፀረ ሽብርተኝነት ጠንካራ አጋርነት እንደ 97 ዓ.ም ብዙም የሚያባብል ካርድ ባለመሆኑ ምክንያት የሃገሪቱ ሁኔታና የመከላከያና ፀጥታ ተቋማት አስካልተናጉ ድረስ አለምአቀፉ ማሕበረሰብ ኢህአዴግ እና አቶ መለስን በስልጣን ለማቆየት ብሎ እንደከዚህ በፊቱ ላይጨነቅና ላይከፋፈል ይችላል፡፡ይህም ሆኖ የአፍሪቃ ቀንድ ፀጥታ እጅግ አሳሳቢ መሆኑ እና ኢትዮጵያ በዚህ አከባቢ መረጋጋት ወይ አለመረጋጋት ላይ ያላት ትልቅ ቦታ አለም አቀፉ ማሕበረሰብ ይገነዘባል፡፡ በዚሁ ምክንያት ቀጣዩ ምርጫ የሃገሪቱ መረጋጋትን፡የመከላከያና ፀጥታ ተቋማት አለመታወክን ባረጋገጠ መልኩ ዳር እንዲደርስ ፍላጐት ይኖረዋል፡፡

ኢትዮጵያ እጅግ ድሃ ከሚባለት እና ድሃ ሃገሮችን ከድህነት የማውጣት ጥያቄ በተነሳ ቁጥር ቀድማ የምትወሳ አገር ናት፡፡ በኢትዮጵያ አስከፊ አገዛዝም ቢኖር እሱን ለመቅጣት ተብሎ ማዕቀብ ማድረግ ህዝበን መቅጣት ስለሚሆን አናደርገውም ባይ ናቸው፡፡ ከገፋነው ወደ ቻይና ጠቅልሎ ይገባል ከሚል ስጋትም መጫኑንና ማራቁን አይወዱትም ይሆናል፡፡ኢትዮጵያ ካለባት ድህነትና የምግብ ዋስትና አለመኖር አኳያ፣ ከምዕራብ ዓለም የሚገኘው የምግብ እርዳታና ፋይናንሳዊ እርዳታ ትልቅ ድርሻ ያለው በመሆኑ፣ የቻይና ድጋፍ ቢመጣም በምንም መልኩ ይህንን ከምዕራብ ዓለም የሚገኘውን ድጋፍ ሊተካ ስለማይችል፣ የኢህአዴግ መንግስት ቻይናን ተማምኖ ከምዕራቡ አለም ይቆራረጣል ተብሎ አይጠበቅም፡፡

እነዚህ እውነታዎች አለም አቀፍ ማሕበረሰበ ሊሄድ የሚችለውንና ከእርሱ ሊጠበቅ የሚችለው ድጋፍ ቁመትና ወርድ ይወስናሉ፡፡

ጠንካራ አማራጭ ሆኖ በመቅረብ፣ ከላይ የተጠቀሱትን እውነታዎች በመገንዘብ የአለም አቀፉ ማሕበረሰብ ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ጉዳዮች እንዲደግፍና እንዲያበረታታ መጠየቅ ይቻላል፡፡

ሀ. ከምርጫ 97 ልምድ በመነሳት የመጪው ምርጫ አስተዳደር፣ የታዛቢዎች ብዛትና ዝርጋታ፣ የኤሌክትሮኒክ ሚዲያ አጠቃቀም፣ አስቸጋሪ የሆኑ ሕጎችን ማስተካከል ወዘተ. በሚመለከት ድርድር ተካሂዶ ምርጫውን በተሻለ ሁኔታ ይካሄድ ዘንድ የራሳቸው ጥረት እንዲያደርጉ መጠየቅ፤ካለፈው ምርጫ በተሻለ አለምአቀፍ ታዛቢዎች እና ዘጋቢዎች እንዲመጡ እና ስለምርጫው ሂደት በሰፊው እንዲታዘቡ፤ እንዲዘግቡ፤ መጠየቅና ማበረታታት ይቻላል፡፡

ለ. በምርጫው ውጤት ላይ የመንግስት ጣልቃ ገብነት እንዳይኖር፣ ቢከሰት ደግሞ አቋማቸውን በማሻያማ መልኩ ይፋ እንዲያደርጉ፤ መጠየቅና ማበረታታት ይቻላል፡፡

ሐ. ከላይ እንደተመለከተው ተፎካካሪው አሸናፊ በሆነበት ሁኔታ፣ስልጣኑ በሰላማዊ መንገድ እንዲረከብ ካልተደረገ በህዝቡና በገዢው ፓርቲ መሃከል የሚፈጠረው ውጥረት የሃገሪቱን ፀጥታና ሰላም ሊያናጋ እንደሚችል በመሬት ላይ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በግልፅ እንዲያዩት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## 4. <u>ሰላማዊና የትጥቅ ትግል ስልቶች</u>

አሁን በሀገራችን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር የስልጣን ሽግግርን በሰላማዊ መንገድ ማምጣት ይቻላል በሚሉና በትጥቅ ትግል ካልሆነ ወይ ትጥቅ ትግልን ካልጨመሩ የስልጣን ሽግግሩ አይቻልም በሚሉ ወገኖች መካከል ክርክሮችና ልዩነቶች አሉ፡፡ ከዚህ በመነሳትም በዚህ ዙሪያ አንዳንድ ጉዳዩች ማንሳት ጠቃሚ ይሆናል፡፡

### 4.1 <u>ትጥቅ ትግል ሲባል</u>:-

ትጥቅ ትግል ሲባል ስለ ማናቸውም ጠበንጃ ያነገበ የፋኖዎች ትግል አይደለም የምንነጋገረው፡፡ በቻይና በቬትናም እንደዚሁም በኢትዮጵያ የታየው እና የዚህ ፅሑፍ አቅራቢ በጥልቀት ስለሚያውቀው ስለተራዘመው የትጥቅ ትግል ነው እየተነጋገርን ያለነው፡፡

የገጠር የትጥቅ ትግል ህዝቡን በስፋት ለትግሉ ማነሳሳት/ ማንቃትንና ማደራጀትን ይጠይቃል፡፡ ማስታጠቅንም ይጨምራል፡፡ ህዝቡ ከጫፍ እስከ ጫፍ መታጠቅ እንዳለበት ይቀበላል፡፡

የገጠር የትጥቅ ትግልን የማቀጣጠሉ ስራ የሚጀመረው በትናንሽ የውግያና የቅስቀሳ ክፍሎች በሚካሄደው ሽምቅ ውግያ ነው፡፡ የሽምቅ ውግያ ወረዳዎቹ ከመንግስት ቁጥጥር ነፃ ሲሆኑ፣ ሽምቅ ውግያው ወደ ሌሎቸ ወረዳዎች ለተመሳሳይ ስራ ሲዘልቅ፣ ከመንግስት ቁጥጥር ነፃ የሆነው አከባቢ ደግሞ ተደራጅቶ በደጀንነት ከመሰለፍ ባሻገር ታጥቆ የአከባቢውን ፀጥታ እንዲጠብቅ ይደረጋል፡፡ በዚህ ሂደት በገጠሩ አከባቢ የትጥቅ ትግሉን ሊደግፍ የሚችል የገጠር መዋቅር ይገነባል፡፡

ሽማቂው ኃይል ማድረግ የሚችለው ሽምቅ ውግያን ማከሄድ ነው በዚህ ብቻ ግን የመንግስትን ሰራዊት ድል መምታትና መንግስትን መለወጥ አይቻልም፡፡ የትጥቅ ትግሉ ግብ የመንግስትን ሰራዊት ድል መትቶ መንግስት መለወጥ ከሆነ ከሽማቂው ሃይል መደበኛ ውግያን ማካሄድ የሚችል መደበኛ ጦር መወለድ አለበት፣ ይህ ሃይል የመንግስትን ጦር በመደበኛ ውግያ ማሸነፍ መቻል አለበት፣ ይህንን ጦርነት ለመደገፍ የሚችል የሎጂስቲክስ አቅም በደጀኑ መገንባት አለበት፡፡ ባጭሩ ጦርነቱን ለማሳከት

የሚያስችል ወታደራዊ ሰትራተጂ እና ስልት መንደፍና እሱን ለስኬት ማብቃት ግድ ይላል፡፡ይሀኛውን የጦርነቱ ክፍል በሚገባ ለመከወን የሚያስችል አቅምና ሁኔታ ከሌለ የሽምቅ ውግያው እዚያው እየተሽከረከረና ራሱን እየደጋገመ ይኖራል እንጂ ለድል ይበቃል ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡

የገጠር የትጥቅ ትግል መሰረቱ ገጠር ነው፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት ከትንሽ ተነስቶ የተደራጀና የታጠቀ ሃይልን የመገንባት ስራ ለማከናወን የሚቻለው የመንግስት ቁጥጥር እና የመንግስት የልማት ተቋማት ደካማ በሆኑበት የገጠር አካባቢ ለመስራቱ ይበልጥ የተመቻቸ ስለሆነ ነው፡፡ በመሆኑም በዛ የመንግስት የቁጥጥር መዋቅር ደካማ በሆነበት ገጠር ተመስርቶ ያንን ደካማውን የመንግስት የቁጥጥር ተቋም እያፈረሱ በሱ ቦታ አማራጭ መዋቅርና ለጦርነት የሚሆን ኢንፍራስትራክቸር መገንባትን ግምት ውስጥ ያስገባል፡፡

የገጠር የትጥቅ ትግል የመንግስት ሰራዊትን ጨምሮ የመንግስት የመግዣ ተቋማትን ማውደምና ማጥፋት እንደ አንድ ዋና ግብ የወሰደ ነው፡፡ እነሱን በማጥፋት መንግስት ህዝቡን የሚገዛበት፣ የሚቆጣጠርበትና የሚያስተዳድርበትን መሳሪያ እንዲያጣ ያደርጋል፡፡ በሌላ በኩል ግን የራሱን ተቋማት በምትክ ይገነባል፡፡ ስለሆነም በገጠር የነበረውን የመንግስት አስተዳደር ሲያፈርስ በእሱ ፈንታ ለትጥቅ ትግሉ ድጋፍ የሚሰጥ የገጠር አስተዳደር ይገነባል፡፡ በገጠር የነበረውን የሰራዊትና የፖሊስ የፀጥታ ኃይሎች መዋቅር ሲጠራርግ በሱ ቦታ ሌሎች የፀጥታ ተቋማትን ይገነባል፡፡ ልማታዊ ተቋማትን ሊጠቀምባቸው ካልቻለ መንግስት እንዳይጠቀሙባቸው ብሎ ያወድማቸዋል፡፡ ሰራዊቱንም እያጠቃና እየደመሰሰ በዚህ ሂደት ሌላ ሰራዊት ይገነባል፡፡

የገጠር የትጥቅ ትግል ወታደራዊ እስትራቴጂ እንዲኖረው ግድ ይላል፡፡ በዚህም የመንግስት ሰራዊት በተራዘመ ሂደት እንዴት እንደሚደመሰሰው ይቀይሳል፡፡ በሱ መትክ ሰራዊት እንዴት እንደሚገነባ ይመልሳል፡፡ ይህ ጦርነት እያካሄዱ የሚደረግ በመሆኑ በጦርነቱ ሂደት ይህንን የመገንባትና የማጥፋት ስራን በተጓዳኝ እንዴት ተደርጎ ስኬት ላይ ለማድረስ እንደሚቻል ይመልሳል፡፡ ይህንን ለማሳካት የሚያስችል የሎጂስቲክ አቅምንም ይመልሳል፡፡ በአጭሩ የገጠር ትጥቅ ትግል እነዚህ ባህሪያት አሉት፡፡

**4.2 <u>ሰላማዊ ትግል</u>:-**

እንደ ትጥቅ ትግል ሁሉ ሰላማዊ ትግልም ህዝብን በስፋት ለትግል ማነሳሳትና ማደራጀትን ግድ ይላል፡፡ ይሄም ሆኖ የታጠቀ ህዝብንና የዚህ አስኳል የሆነ ሰራዊት መገንባትን አይጠይቅም፡፡ ሰላማዊ ትግል መንግስት የሚኖረው የህዝቡ እሺታና ትብብር እስካገኘ ድረስ ነው፣ህዝቡ ለመንግስት ይሰጠው የነበረውን እሺታና ፈቃደኝነት ከነፈገ

ግን መንግስት ሆኖ መቀጠል አይቻለውም ከሚል እምነት ይነሳል (1) ። ለዚሁም ህዝቡን ለትግል ይቀሰቅሳል ያደራጃልም። ይህን የሚያደርግው ግን ትጥቅ ትግል ጋ እንደሚደረገው ለጦርነትና ለአመፅ ሳይሆን የተደራጀው ህዝብ ለገዢዎች ይቸር የነበረን እሺታና ታዛዥነት የነፈገ ህዝብ እንዲሆን፣ገዢዎች ህዝብ ሰጥ ፀጥ ብሎ እንዲገዛላቸው በመሳሪያነት የሚጠቀሙትን የስነ-ልቦና እና የአካል ማስፈራሪያዎች የማይበግረው ፍርሀትን ያሸነፈ ህዝብ እንዲሆን፣ ነው።ሰላማዊ ትግል የታጠቀ ሰራዊትና ህዝብ በመፍጠር ፈንታ ጉልበት መጠቀምን እምቢ የሚል ግን ለጉልበት የማይመች ግዙፍ የእምቢታ ኃይልን ያደራጃል።

ሰላማዊ ትግል በገጠርም በከተማም ይካሄዳል። ያም ሆኖ ማእከሉ ከተማ ነው። የገዢዎች የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማእከል ከተማ እንደመሆኑ መጠን ሰላማዊ ትግሉም ከዛ ማእከል ነው የሚጀምረው። ዘመናዊ የመገናኛ ዘዴ የተስፋፋበት ብዙ ህዝብ በተቀራራቢ ሁኔታ የሚኖርበት መልእክቶችን ለብዙ ህዝብ በአጭር ጊዜ ለማዳረስ የሚቻልበት ከመሆኑ አኳያ ሰላማዊ ትግል ማእከሉ ከተማ እንዲሆን ግድ ይላል። ማእከሉ ከተማ አድርጎ ግን በዛ አይወሰንም። ከከተማ ወደ ገጠር ይዘልቃል ስለሆነም ሰላማዊ የትግል ስልት ገጠርንም ያዳርሳል።

ሰላማዊ ትግል የበለጠ ውጤታማ ሊሆን የሚችለው ውሱንም ቢሆን ለዚሁ አመቺ የሆነ ፖለቲካዊ ምህዳር ሲኖር ነው። የፖለቲካ ምህዳር ግን ተነፃፃሪ ነው። እንደ ሀገሩ ሁኔታ እና የዲሞክራሲ እድገት ሊሰፋ ወይም ሊጠብ ይችላል። ይሄ አንድ ነገር ሆኖ ሰላማዊ ትግል ሁሉ ጊዜ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ምህዳር መኖሩን ግድ ይላል ማለት አይደለም። አፋኝ አገዛዞች ባሉበት ሁኔታም ይካሄዳል፣ ተካሂዶም አፋኝ አገዛዞችን ከስልጣን ማስወገድ እንደሚቻል ታይቷል።

### 4.3 <u>የሁለቱም ንፅፅር</u>

የትጥቅ ትግልም ሆነ ሰላማዊ ትግል ህዝብን በስፋት በማነሳሳትና በማደራጀት ላይ ይስማማሉ። ይሄን የፖለቲካ ለውጥ ሊያመጣ በሚችል ደረጃ ለማሳካትም ጊዜ እንደሚጠይቅ ሁለቱም ይገነዘባሉ። በዚህ ላይ ስምምነት ቢኖራቸውም ህዝቡን የሚያነሳሱትና የሚያደራጁት ግን ለተለያየ ፍልሚያ ነው።

ሁለቱም ጋር ያለ ልዩነት በሶስት ጉዳዬች ላይ አተኩሮ ማየት ጠቃሚ ይሆናል።

አንደኛውና ዋናው ልዩነታቸው በሰራዊት ላይ ያላቸው ልዩነት ነው። የትጥቅ ትግል የመንግስትን ሰራዊት እንደ ዋና ዕንቅፋትና እንደ ትልቁ መወገድ ያለበት መሰናክል

....................

*1.* The Unconquerable World, Jonathan schell p.128-130

ይወስዳል፡፡ በዚህም ምክንያት ሰራዊቱን በመደምሰስ ላይ ያነጣጥራል፡፡ ህዝቡን ማነሳሳትና ማደራጀትም ከዚህ አኳያ የተቃኘ፣ማሳረጊያውም የትጥቅ ትግሉን ማፋፋም፣ ጦርነቱን መደገፍ፣ ሰራዊትና የታጠቀ ህዝብን መገንባት፤ ይህንንም አቀነባብሮ ሰራዊትን በጦር ሜዳ ማሸነፍ ይሆናል፡፡

ሰላማዊ ትግል የሚነሳበት እሳቤ እጅጉን የተለየ ነው፡፡ መንግስት የሚኖረው የህዝብ እሺታና ታዛዥነት እስካለ ነው፡፡ የህዝብ እሽታና ታዛዥነት ካለ ስርዓት ይኖራል መንግስትም የፈለገውን በስርዓት ማከናወን ይቻለዋል፡፡ የህዝቡ እሽታና ታዛዥነት የተነፈገው መንግስት ግን የህዝቡን ፍሰት የህዝቡን እንቅስቃሴና የሃገሪቱን ሂወት እሱ በፈለገው መልክ ሊመራ አይችልም፡፡ እምቢ ያለንና ፍርሃትን ያሸነፈ ህዝብ ይዞ መንግስት ሆኖ መቀጠል አይችልም፡፡

ለሰራዊት እና ለፀጥታ ኃይሎች ታዛዥነት መሰረቱ የህዝቡ እሺታና ታዛዥነት ነው፡፡ ያለ የህዝቡ እሺታና ታዛዥነት የእነዚህ ተቋማት ታዛዥነት ብቻውን የሚፈይደው አይኖርም፡፡እነዚህ ተቋማት ወጤት የሚያመጡት የእነሱን ሃይልና ጉልበት የሚፈትን እንደነሱ ጉልበት ለመጠቀም የቆረጠ ተፎካካሪ ሲመጣባቸው ነው፡፡ ፍርሃትን ያሸነፈ ግን ደግሞ ሃይልን በሃይል ለመመለስ ፈቃደኛ ያልሆነ አይበገሬ ህዝብ ላይ እነዚህ ብቻቸውን የሚያመጡት ለውጥ አይኖርም፡፡

በሰላማዊ ትግል ህዝቡን የማነሳሳትና የማደራጀት ስራ ሲሰራ ህዝቡ በቃኝ አልገዛም እንዲል ከማድረግ አኳያ ነው፡፡ይህንን በምርጫ እንዲገልፅ የማነሳሳት እና የማደራጀት ስራ ይካሄዳል፣ህዝቡ ፍርሀቱን ነቅሎ እንዲያወጣ የሚያስችለው በበርካታ የትግል ስልቶች እንዲያልፍና እንዲለማመዳቸው ያደርጋል፣ይህ ከሆነ ደግሞ መንግስት ያ ግዙፍና በጣም አስፈሪ ነገር መሆኑ ያበቃል፡፡ሰላማዊ ትግል ከዚህ እሳቤ ይነሳል፡፡

በሁለቱ መሀከል ያለው ሁለተኛው ልዩነት የሚያስከፍሉት ዋጋ ላይ ያለው ልዩነት ነው፡፡

በገጠር የትጥቅ ትግል መርህ፣ለትጥቅ ትግሉ ስኬት የማያገለግል፣መንግስት ለሚያካሂደው ጦርነት ግን የሚያገለግል ነገር ሁሉ ይወድማል፡፡ መኪና የማትጠቀምበት ከሆነ ታቃጥለዋለህ፡፡ የመገናኛ አውታሮች የማትጠቀምባቸው ከሆነ እንዳይሰሩ ታደርጋቸዋለህ፡፡ በዚህ መንገድ ብቻ የሚወድም የሃገር አቅም ትልቅ ነው፡፡ ከዛ አልፎ ሁለቱም ወገኖች በቁጥጥራቸው ስር ያለውን የሀገር ኢኮኖሚ የሚያካሂዱትን ጦርነት ለመቀለብ ያውሉታል፡፡ አምራች ጉልበትም ከማምረት ስራው ተፈናቅሎ ለጦርነቱ እንዲከት ይደረጋል፡፡ ይህ የሚያስከትለው ኢኮኖሚያዊ ውድመት ይሁን በሂወት ረገድ የሚያስከትለው ዋጋ በጣም ብዙ ነው፡፡ የኢኮኖሚው ውድመትና በሰው ሂወትና አካል የሚደርሰው ጥፋት ከፍተኛ ማህበራዊ ቀውሶችን ይፈጥራሉ፡፡ ኋላ ላይ እነዚህን

ለመጠገን የሚጠይቀው ጊዜና የሚያስከፍለው ዋጋ በጣም ትልቅ ከመሆኑ ባሻገር አንዳንዶቹ ጉዳቶች ለመጠገንና ለማከም ጨርሶ የማይቻሉ ሊሆኑ ይችላሉ።

በሰላማዊ ትግል ለጉልበት እምቢ ማለት አለ። ይህንን የህዝብ እምቢታ ለመስበርና በምትኩም ፍርሀትን ለማንገስ መንግስት የሚወስዳቸው እርምጃዎች መኖራቸው አይቀርም። ሰዎች ሊታሰሩ ሊደበደቡና አካላቸው ሊጎዳ ይችላል። ከዛም አልፎ ሞትም ሊኖር ይችላል። ትግሉ እየከረረ በሄደ ቁጥርም ሽብርን ለማንገስ ተብለው የሚወሰዱ ጨካኝ እርምጃዎች እየበዙ ሊሄዱ ይችላሉ። በትግሉ በኩል በሚፈፀሙ የስልት ስህተቶችም ያልተፈለገ ጉዳት በህዝቡ ላይ ሊደርስ ይችላል። ሰላማዊ ትግል ሰላማዊ ነው ስለተባለ ችግርና መከራ የለበትም ማለት አይደለም። ያም ሆኖ ጦርነት ከሚያስከፍለው ዋጋ አንፃር ሲታይ ግን ሰላማዊ ትግል የሚያስከፍለው ዋጋ አነስተኛ ነው ብሎ ደፍሮ መናገር ይቻላል።

ሶስተኛው የሚለያዩበት ነጥብ ውጤታማነታቸው ላይ ነው፡- አንድን መንግስት ከስልጣን በማስወገድ በኩል ሁለቱም ያስኬዳሉ ማለት ይቻል ይሆናል። ዴሞክራሲ ከማስፈን አኳያ ግን እኩል ያስኬዳሉ ማለት አይቻልም ብቻ ሳይሆን የትጥቅ ትግል ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ማስኬዱ ላይ ትልቅ ጥያቄ ምልክት አለ። ለዚህም ምክንያት አለው።

ጦርነት ህዝብ ይቀሰቅሳል፣ ህዝብ ያደራጃል፣ያስታጥቃል፣ ግን ደግሞ ይሄ የተደራጀና የታጠቀ ህዝብ የፖለቲካ ጨዋታውን የሚያካሄደው በጦር መሳሪያ አጀብ በመሆኑ ፖለቲከው በብዙ መልኩ ሰብአዊ ገፅታው የደከመ፣ክፋትና ጭካኔም የተላበሰ ፖለቲከ እንዲሆን፣ ነገሮች ከተለመደው ሰብአዊ ግንኙነት ውጪ እንዲሄዱ፣ያደርጋል(1)። የፖለቲካ አላማው የሚገፋው በመጋደል በደም መፋሰስ እንደመሆኑ፣ የጦር መማዘዙንና ደም መፋሰሱን ህይወትና ስነልቦና፣ ከጦር ክፍሎች ውጪ ወደ ሕብረተሰቡ እንዲጋባ ያደርገውና፣ ሕብረተሰቡ እንደ ሕብረተሰብ ለሰብአዊ መብት፣ ለዴሞክራሲያዊ መብት፣ ለውይይት፣ ለሃሳቦች ነፃ ሽርሽር እና ለመቻቻል፣ ያለው ዝግጁነት እጅግ ደካማ እንዲሆን አስተዋጽኦ ያደርጋል። እንደዚህ ባለ ሕብረተሰብ ዴሞክራሲ እንዲያብብና እንዲያድግ ማድረግ ኣስቸጋሪ ያደርገዋል።

### 4.4 ለኢትዮጵያ የሚበጀው ሰላማዊ ስልት ስለመሆኑ :-

የዚህ ፅሑፍ አቅራቢ የትግል ልምድ ለትጥቅ ትግል ያደላ ቢሆንም ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታና አሁን ካለንበት አለማዊ ሁኔታ አኳያ ግን በኢትዮጵያ ከትጥቅ ትግል

................

*1.* Jonathan Schell, Ibid p. 83

ይልቅ ሰላማዊ የትግል ስልት ውጤት ያመጣል የሚል እምነት አለው:: በንፅፅሩ ላይ የተመለከቱት እንዳሉ ሆነው ከአለንበት አጠቃላይ አለማዊና የአገራችን ሁኔታ አኳያም መመልከቱ ተቃሚ ይሆናል::

**4.4.1 <u>አለማቀፋዊ ሁኔታ</u>:-**

የቀዝቃዛው ጦርነት ዘመን ለትጥቅ ትግልና ለጦር መሳሪያ ዝውውር አመቺ ነበር ማለት ይቻላል::አለም ለሁለት ተከፍሎ በከፍተኛ ፉክክር ውስጥ በገባበት ወቅት « የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው» ከሚል መርህ አንዱ ሌላውን ለማዳከም ጦር መሳሪያን በገፍ የሚያቀብልበት፣እንደዚሁም አንዱን ለማዳከም አስፈላጊ የሆኑት ድጋፎች ከሌላው ለማግኘት የሚቻልበት ሁኔታ በመኖሩ፣ ጦር መሳሪያው ወይም ሎጂስቲክሱና መሸመቻው ስለሚገኝ የትጥቅ ትግል የሚጠይቀውን ከፍተኛ የጦር መሳሪያና የሎጂስቲክስ አቅርቦት ለመወጣት የተሻለ ዕድል ነበር ለማለት ይቻላል::ቀዝቃዛው ጦርነት ካበቃ ወዲህ ይሄ ነገር ለማግኘት የነበረውን እድል በከፍተኛ ደረጃ አጥብቦታል:: ለትጥቅ ትግልና ለጦር መሳሪያ ዝውውር የነበረው አመቺ ሁኔታም እየተጣበበ ነው:: አሁንም ገንዘብ ባይጠፋም የጦር መሳሪያ ሸመታም ጠፍተዋል ባይባልም ሰራዊት ገንብቶ ሌላን ሰራዊት በጦር ሜዳ በፍልሚያ ለማሸነፍ የሚያስችል የገንዘብ አቅምና የመሳሪያ ፍሰት የሚገኝበት ሁኔታ የለም:: እንዲያውም በአለም አቀፍ ደረጃ የትጥቅ ትግል ማካሄድ ከሽብርተኝነት ጋር ተደርቦ የሚፈረጅበትና የሚወቀስበት ሁኔታ ነው ያለው::

ይልቁኑስ አሁን ባለው የአለም ሁኔታ ሃሳብን የመግለፅ ነፃነትን ለማረጋገጥ፣ የመምረጥና የመመረጥ ነፃነትን ለማረጋገጥ፣ ተደራጅቶ መብትንና ጥቅምን በሰላማዊ መንገድ ለማስጠበቅ፣ወዘተ ለሚደረገው ትግል ከፍተኛ አለማቀፋዊ ድጋፍ አለ ለማለት ይቻላል::

ዘመኑ የነፃ ፉክክር፣ የነፃ ገበያ፣ የነፃ ውድድር፣ የነፃ ሃሳብ የመግለፁ እና የመንቀሳቀስ መብት ዘመን፣ የሰብአዊ መብቶች መከበር ዘመን፣ እየሆነ በመምጣቱ የተገፉ ወገኖች ይቅርና ለይስሙላም ቢሆን አምባገነኖችም ይህንን መፈክር አንግበው በዚሁ ስር እያደናገሩ ለመኖር የሚጣጣሩበት ወቅት ላይ ነው ያለነው:: ይህንን በጎ አለማአቀፋዊ እውነታ ላይ ተመርኩዞ በገዛ ሀገር ነፃነትን ለማስፈን ሰላማዊ ትግል ማካሄዱ የበለጠ ድጋፍ ያስገኛል::

ይህንን አስተሳሰብ ለማራመድ የአለም አቀፍ ተቋማት ድጋፍ ማግኘት ይቻላል:: የተባበሩት መንግስታት ሳይቀር ሃሳብን ለመግለፅ፣ለመምረጥና ለመመረጥ፣ነፃና ዴሞክራቲክ ምርጫ ይኖር ዘንድ፣የመድብለ ፓርቲ ስርዓት እንዲኖር፣ የፖለቲካና የሞራል ድጋፍ ይሰጣል:: ለሰዎች ሰብአዊ መብት ጥበቃና ሃሳብን በነፃ የመግለፅ መብት

ጥበቃ የቆሙ አለም አቀፍ ድርጅቶች ያሉበት፣ አፋኝ አገዛዞች አደብ እንዲገዙ የሚጮሁ ከዛ አለፍ በሎም ፍ/ቤት አቅርበው እስከ ማስቀጣት የሚሄዱ አለም አቀፋዊ ተቋማት ብቅ ያሉበት ወቅት ላይ ነን:: ይህ ባለበት ለሰላማዊ ትግል አመቺ አለማዊ ሁኔታ አለ ማለት ይቻላል::

ዘመኑ ያመጣው የመረጃ ቴክኖሎጂ ዕድገት አለ:: ግፍ ተፈፅሞ ሊሰወር የማይቻልበት፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ በአለም አቀፍ ደረጃ ሊሰራጭ የሚችልበት፣ ስለሆነም ግፈኛ መንግስታትንና ግፈኛ ተግባራቸውን ለማጋለጥ የሚቻልበት፣ ሃሳብና መረጃ ከመቼውም ጊዜ በተሻለ መልኩ ለህዝብ ለማድረስ የሚቻልበት ሁኔታ ላይ ነን ያለነው:: ይህንን የቴክኖሎጂ ዕድገት ህዝበብን ለመቆጣጠር እና ለዚህ አፋኝ አላማ የመጠቀም ሁኔታ ያለ ቢሆንም፣ ይህንን ለመግታት ሙከራ ያለ መሆኑ ቢታወቅም፣ ይሄን ዘመን ያመጣው ጉርፍ ተቋቁሞ እሱ የሚያመጣውን ጥቅም ለመቋቋም ግን የሚያስችላቸው አይደለም:: ስለሆነም ከላይ በተገለፁት ምክንያቶች፣ አለም አቀፋዊ ሁኔታው ከማንኛውም ጊዜ በበለጠ ለሰላማዊ ትግል የተመቸ ነው::

**4.4.2 ሰላማዊ ትግል በሀገራችንም ህገ መንግስታዊ ድጋፍ አለው:-**

የኢፌዲሪ ህገ-መንግስት ለመሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች እውቅናና ጥበቃ ሰጥቶአል:: ኢህአዴግ እነዚህን መብቶች የሚያጠቡ ተፃራሪ ህጎችና አስራሮች እየተጠቀመ መሆኑ እንደተጠበቀ፣ ሆኖ በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው መብቶች ከመሆን አልፈው በሀገራችንም ህገ-መንግስታዊ ድጋፍ ያላቸው መሆኑና እነዚህን ተጠቅሞ ሰላማዊ ትግል ማካሄድ ወንጀል ሆኖ የማያሳስር፣ የማያስገድል፣ መሆኑ ተገቢው ግንዛቤ ሊሰጠው የሚገባ እውነታ ነው::

እንደዚህ ባለ ሁኔታ ላይ ያሉ ፖለቲከኞች ሊከተሉት የሚገባው የትግል ስልት፣ ያሉት የህግ ቀዳዳዎች እንዳይጠቡ ይልቁንስ እንዲሰፉ በህዝብ መሃል ሆነው ከህዝብ ጋር መታገል ነው መሆን ያለበት? ወይስ እነዚህ አይበቁም፣ አይሰሩም፣ አያስሩም፣ ጠበዋል ብሎ እነሱን ትቶ ወደ ትጥቅ ትግል መሄድ ነው የሚሻለው? ነው ዋናው ጥያቄ::

በዚህ ፅሁፍ አቅራቢ እምነት እነዚህ ቀዳዳዎች አልበቁም ብሎ የትጥቅ ትግል አማራጭን መውሰድ ያሉትም ጨርሰው እንዲዘጉ ያደርጋል እንጂ ዴሞክራሲን አያጠናክርም አይመልስም፣ ይልቁንስ ከሰላማዊ ዴሞክራሲያዊ ሂደት የሚወጡቱ መውጣታቸው በራሱ ለዴሞክራሲ መጥበብ ምክንያት ሊሆን ይችላል የሚል ስጋት አለው::

እነዚህ መብቶችና ነፃነቶች የመላ ኢትዮጵያዊያን መብቶችና ነፃነቶች ናቸው:: የተወሰነ የሕብረተሰብ ክፍል መብቶች አይደሉም::ሃሳብን የመግለፅ መብት የሁሉም ዜጎች መብት እንጂ የጋዜጠኞች ብቻ አይደለም:: ይህም ሆኖ ግን ሃሳብን የመግለፅ

መብት የፕሬስ መብት ብቻ ተደርጎ ይታያል፡፡ ለዚህም ጋዜጠኞች እና የመንግስት ባለስልጣናት ብቻ ባለጉዳይ ተደርገው የሚታዩበት ሁኔታ አለ፡፡በተመሳሳይ መልኩ የመደራጀት መብት የተወሰኑ ሲቪክ ድርጅቶችን ብቻ የሚመለከት፣ነፃ ምርጫ ነክ ጉዳዮችን ደግሞ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ብቻ የሚመለከት አድርጎ የመመልከት ሁኔታ አለ፡፡

ይህ ጠባብ የነፃነቶች ግንዛቤ አብዛኛው ሕብረተሰብ ተመልካች፣ የተወሰኑ ክፍሎች ብቻ ተሚጋች የሚሆኑበት እና መብቶቹ የምልአተ ህዝቡ ዋና አጀንዳ ከመሆን እየወጡ የሚታዩበት ሁኔታ እየፈጠረ ነው፡፡ኢህአዴግ የሚያካሂደው ምህዳሩን የማጥበብ ዘመቻ ህገመንግስቱን ተደግፎ መከላከል ይቻላል ይገባልም፡፡ ይህንን ከማሳካት አኳያ እነዚያ ተሚጋች ክፍሎች የተባበረ ትግል ማካሄድን መልመድ ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚያም አልፎ ህዝቡ ትግላቸውን እንዲቀላቀል እና ባለቤት መሆኑን በተግባር እንዲያረጋገጥ፣ በህዝቡ መሀል ተገኝቶ ማስተማር በየቀኑም እንዲጠቀምባቸው ማለማመድ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በኢህአዴግ በኩል የፖለቲከ ምህዳሩን የማጥበብ ዘመቻ ቢኖርም መፍትሄው በሕብረተሰቡ መሀል ተገኝቶ እነዚህን የህገ-መንግስታችን ድጋፍ ያገኙትን መብቶች ህዝቡ የራሱ እሴቶች እንዲያደርጋቸው መታገልና ለዚሁ ማብቃት እንጂ ከዚሁ ወጥቶ ወደ ትጥቅ ትግል መሄድ አይሆንም፡፡ ከዚህ ወጥቶ ወደ ትጥቅ ትግል መሄድ እየጠበበ ያለውን የፖለቲከ ምህዳር የበለጠ እንዲያጠበው፣ ኢህአዴግን ያመቻችለታል፡፡ ሕብረተሰቡም በዛ በኩል ገብቶ እንዳይማርና የግሉ መብቶች እንዳያደርጋቸው እንቅፋት ይሆናል እንጂ አይደግፈውም፡፡

## 5. <u>የ ሰላማዊ የትግል መልኮችና መርሆዎች</u>

ስለ ሰላማዊ የትግል መልኮች ጥልቅ ጥናቶች ካደረጉት አንዱ ጂን ሻርፕ ሲሆን በዚህ ጉዳይ በርከት ያሉ ፀሑፎች ፅፎኣል፡፡ ከነዚህ አንዱም ወደ አማርኛ ተመልሶአል፡፡ ስለ ሰላማዊ የትግል መልኮችና ዘዴዎች ሰፋ ያለ ግንዛቤ ለማግኘት እነዚህን ማጥናት እና መዳሰስ ይመከራል፡፡

የሰላማዊ ትግል መልኮችና ዘዴዎች ዝርዝር ረዥም ቢሆንም ሁሉም የትም ቦታ ይሰራሉ ማለት አይደለም፡፡ እንደየሃገሩ ሁኔታ እንደየትግሉ ግብና እንደባለጉዳዮቹ ማንነት የሚመረጠው የትግል መልኮችና ዘዴዎች ቀመር ሊለያይ ይችላል፡፡በመሆኑም በዚህ ፅሑፍ የሚሰነዘሩት ነጥቦች የሰላማዊ የትግል መልኮችን በሚመለከት አጠቃላይ ግንዛቤ ከማስቀመጥ ያለፈ ፋይዳ እንደሌላቸው ሊጤን ይገባዋል

### <u>5.1. ሰላማዊ የትግል መልኮች እና ዘዴዎች</u>

ፈረንጆች ሲተርቱ "Necessity is the mother of invention" ይላሉ፡፡ ፍላጎቱ እና ጥያቄው ተለይቶ እና ገፍቶ ከመጣ መፍትሄው መፍለቁ አይቀሬ ነው ለማለት ነው፡፡ የትግል መልኮችም በዚሁ ምሳሌ ሊታዩ ይችላሉ፡፡

ሰዎች አንድን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖምያዊ ወይም ማህበራዊ ችግር እናርም ብለው ከወሰኑ እና ከቆረጡ ለዚሁ መዳረሻ ስልቶች መፈለግ እና ማፍለቅ ላይ ከጭንቅላታቸው በስተቀር የሚገድባቸው ሃይል ኣይኖርም፡፡ ስልቶች በየጊዜው እንደየሁኔታው አስገዳጅነት የሚፈልቁና የሚዳብሩ የትግል ምርቶች ናቸውና ተዝርዝረው አያለቁም፣ በየጊዜውም ኣዳዲስ ይወለዳሉ፡፡

ጄን ሻርፐ እስካሁን የደረስኩባቸው እና ያወቅኩዋቸው መቶ ዘጠና ስምንት የሰላማዊ ትግል ዘዴዎችና ስልቶች አሉ ይላል ይህን ሲል ግን ያለደረሰባቸው ግን ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉ ሊኖሩ እንደሚችሉ ወደፊት ሊፈልቁ የሚችሉ ኣዳዲስ ስልቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ በመገንዘብ ይህ ዝርዝር ያለቀለት አለማሆኑን ያስገነዝባል፡፡ለአጥኚዎች እንዲመች በሎም ከአጠቃላይ ባህርያቸው አንፃር እነዚህ ስልቶች በሶስት ዋና ዋና ምድቦች ያስቀምጣቸዋል (1)

ሀ. ድጋፍ መንሻ፣ መስጫ እና ማነሳሻ ስልቶች

ለ. የትብብር መንፈግ እና አሻፈርኝ የማለት ስልቶች

ሐ. የሰላማዊ ጣልቃገብነት እና ተነሳሽነት ስልቶች

ከመቶ ዘጠና ስምንቱ ውስጥ አምሳ ኣራቱን መጀመርያው ምድብ ላይ፣ መቶ ሶስቱን ሁለተኛው ላይ፣ አርባ ኣንዱን ደግሞ ሶስተኛው ምድብ ላይ አስቀምጦኣቸዋል፡፡

የሶስቱን ምድቦች አጠቃላይ ባህርያት እንመልከት

## 5.1.1. ድጋፍ መንሻ እና መስጫ ማነሳሻ ስልቶች

ስለ ድጋፍ መንሻ፣መስጫ እና ማነሳሻ ስልቶች ምንነት በቀላሉ ለመግንዘብ በአሜሪካው የሁለት ሺ ስምንት ፕረዚዳንታዊ ምርጫ ተፎካካሪዎች የተጠቀሙባቸውን ስልቶች መመለከት ይበቃል፡፡

ሴነተር ክሊንተን የዴሞክራቲክ ፓርቲ እጩ ሆነው ለመቅረብ ይበቁ ዘንድ ከሴነተር ኦባማ ጋራ የምረጡኝ ትንቅንቅ ውስጥ በገቡበት ወቅት ብልጫየ ብለው የቀሰቀሱበት ነጥብ የጦር ሃይሎች ጠቅላይ ኣዛዥ ለመሆን ያላቸው ተነጻጻሪ ዝግጁነት የበለጠ መሆኑን ነበር፡፡ ከሴኔተር ኦባማ ይልቅ እኔ እሻላችሁአለሁ ብሎ ድጋፍ ለመሻት በዚህ ነጥብ ዙርያ በርካታ የማነሳሻ ስልቶች ተጠቅመዋል፡፡ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥተዋል፣ በህዝባዊ ስብሰባዎች በሰፊው ተናግረውበታል፣ ከሴናተር ኦባማ ጋር ፊትለፊት በተደረገ ክርክር ተናግረውበታል፣ የታወቁ ሰዎች በዚህ ጉዳይ ‹‹እውነታቸውን ነው እርሳቸው ይበልጥ ዝግጁ ናቸው›› ብለው እንዲናገሩላቸው አድርገዋል፡፡ ከሁሉም ስልቶቻቸው የብዙ ሰዎችን ቀልብ የሳበው ስልታቸው ደግሞ በዚሁ ጉዳይ በቴሌቪዥን ያሰራጩት the three o'clock call የተሰኘው አጭር የምረጡኝ ማስታወቂያቸው ነበር፡፡ በዚህ ክሊፕ መላ ኣሜሪካ በተኛበት ውድቅት ሌሊት ላይ ዋይት ሃውስ ቤተመንግስት ዘንድ በሌላኛው የአለማችን ጫፍ ላይ የተከሰተ አንድን ትልቅ አደጋ አስመልክቶ የኣደጋ የስልክ ጥሪ ሲደወል ይሰማል፣እንደዚህ ባለ ድንገተኛ ሁኔታ ላይ ብቃት ያለው ቅጽበታዊ ምላሽ መስጠት የሚችለው ኦባማ ሳይሆን እኔ ነኝ ብለው መልእክቱን ይቋጫሉ፡፡

በዚሁ የምረጡኝ ፉክክር ለአንዱ ድጋፍ ለመሻት ለሌላው ደግሞ ድጋፍ ለመንሳት የሚያስችሉ የተባሉ በርካታ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል፣ መልእክት ያዘሉ

.............

1. Waging Nonviolent Struggle 20th century practice and 21st century potential, Gene Sharp p50

ባርኔጣዎች፤ቲሸርቶች፤ባጆች፤ሰቲከሮች፤ፖስተሮች፤በራሪ፤ወረቀቶች፤ወዘተ ተሰራጭተዋል፡፡ ኮሜድያኖች በጨዋታ እና በማስመሰል ድራማዎች መልክቶች እንዲያስተላልፉ ተደርገዋል የካርቱን ሙያተኞች ሙያቸውን ለዚሁ ዘመቻ አበርክተዋል፡፡

እነዚህ ድጋፍ ለመሻት ወይ ለመንሳት ከሚደረጉት የማነሳሻ ስልቶች ሊጠቀሱ የሚችሉ ጥቂት ምሳሌዎች ናቸው፡፡ የነዚህ ስልቶች ፋይዳ መልእክት ማስተላለፍ ሆኖ የሚተላለፈው መልእክት ግን የተቃውሞ ወይም የድጋፍ ሊሆን ይችላል፣አንድን ሁኔታ( ለምሳሌ ከዚህ በፊት የተፈፀመን ግፍ) ለመዘከርና ለማስታወስ ያለመም ሊሆን ይችላል፡፡ የመልእክቱ ተደራሽ መንግስት፣መራጭ፣የአንድ የንግድ ድርጅት ሹማምንት፣የአንድ ከተማ ከንቲባ፣ሰራተኞች፣ ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ መልእክቱን የሚያስተላልፉት ደግሞ ግለሰቦች፣ ፓርቲዎች፣ ተበዳይ ወይም ተቆርቋሪ ወገኖች ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ መልእክቱ የሚተላለፈው በፅሁፍና ንግግር የታጀበ የተለያየ ቅርጽ ያለው መግለጫ ሊሆን ይችላል፣በብዙ እንቅስቃሴ እና ትእይንት የታጀበ የአደባባይ ሰልፍም ሊሆን ይችላል፡፡

በዚህ ምድብ ውስጥ በአንድ ጉዳይ ላይ ተቃውሞ ለማሰማት፤ እወቁልኝ ስሙልኝ ብሎ ሌሎችን ለማሰማት፤ተቃውሞ ያስነሳው ጉዳይ የሚያስከትለው ጉዳት ምን እንደሆነ ለሚመለከታቸው አስረድቶ እርምጃቸውን እንዲቀለብሱ ወይም እንዲያስተካክሉ ለማሳመን፤ ካልቀለበሱ ደግሞ ሊከተል የሚችለውን እርምጃ ለማመልከት፤ ተበዳይ ወገኖች ብቻቸው እንዳልሆኑ ደጋፊ እንዳላቸው ለማሳየት የሚደረጉት ስልቶች በሙሉ ይጠቃለላሉ፡፡ በዚህ ክፍል የሚጠቃለሉት ስልቶች ከላይ እንደተገፀው አምሳ ኣራት ያህል ቢሆኑም ሁሉንም የሚያመሳስላቸው አንድ ባህርይ፤ እንዲተላለፍ የተፈለገው መልእክት ለተደራሹ ወገን ግልፅና በሚያሳምን መልኩ መቅረቡ፤ በዋናነት የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የድጋፍ ወይም ተቃውሞ ሃይል እና አድማስ ማሰፋፍያ ስልቶች መሆናቸው እና ከዚህ ኣልፈው ወደ አለመተባበርና ጣልቃ ገብነት አለመሸጋገራቸው ነው፡፡

በተለምዶ ተቃውሞ ወይም ድጋፍ መንፈግ የሚገለፅባቸው ስልቶች መግለጫ ስብሰባ እና ትእይንቶች እና ሰልፎች ብቻ አድርጎ የማየት ሁኔታ ኣለ፣ የዚሁ ተፃራሪ የሚመስሉ ስልቶችም ግን የተቃውሞ መግለጫ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ስብሰባን ለምሳሌ ብንውስድ ተቀዋሚዎቹ ስብሰባ ጠርተው እና ተመካክረው የኣቋም መግለጫ ሊያወጡ ይችላሉ ይህን ለማድረግ ባይቻል ፊርማ አሰባስቦ ከጉዳዩ በስተጀርባ አያሌ ዜጎች እንዳሉም ማሳየት ይቻላል፣ የሚቃወሙት መንግስት ለራሱ አላማ ብሎ ለስብሰባ ቢጠራ ስብሰባውን በተለያየ መልኩ ለጠሪው ለራሱ ያለውን ተቃውሞ መግለጫ ማድረግ ይቻላል፡፡ በስብሰባው ላይ ተገኝቶ ሊጀመር ሲል ረግጦ መውጣት ፣ አንሰማም ለማለት ጆሮን በእጅ ማፈን፣ ለመድረኩ ጀርባ ሰጥቶ መቀመጥ ወይም የውውይቱን ኣቅጣጫ ማስቀየር ይቻላል፡፡

## 5.1.2. የትብብር መንፈግና አሻፈረኝ የማለት ስልቶች

ኣንድ ግለሰብ፣ተቋም ወይም መንግስት ለሚያራምዳቸው ኣቋሞችና ለሚፈፅቸው ድርጊቶች ሌሎች ወገኖች ያላቸውን ተቃውሞ ለመግለፅና ለማሳየት ተብሎ የሚደረጉ፤ የተለመደውን ግንኙነት እና ትብብር በጠቅላላ፣በከፊል ወይም በፊት በነበረው ደረጃና መልክ ላለመቀጠል መወሰንን የሚመለከቱ ስልቶች ናቸው በዚህ ክፍል የሚጠቃለሉት። የሚነፈገው ትብብር በይዘቱ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ወይም ሁሉን አቀፍ ሊሆን ይችላል። እርምጃው እንደየሃገሩ ሁኔታ ህጋዊ ሊሆን ላይሆን ይችላል፣ ግን ሰላማዊ ነው።

ትብብርን የመንፈግና አሻፈርኝ የማለት ስልቶች የሚነሱበት መሰረተ ሃሳብ መንግስታት፣ ድርጅቶችና ግለሰቦች የፈለገውን ገንዘብና መሳሪያ ቢኖራቸውም ከህብረተሰብ ተለይተውና ተነጥለው ሊኖሩ ኣይቻላቸውም የሚል ነው።

አሜሪካ በጣም ሃያል ሀገር ብትሆንም የዓለሙ ማህበረሰብ ኣካል ናትና የዓለሙ ማህበረሰብ ትብብር ከነፈጋት በማእቀብና በውግዘት ተከባ ብቻዋን መዝለቅ አትችልም። ከአሜሪካ ደከም ያሉት አገሮች ላይ ሲመጣ ደግሞ ውግዘቱ እና ማእቀቡ የከፋ ወጤት ያስከትላል። የአንድ አገር መንግስትም ቢሆን የተለመደ መንግስታዊ ስራውን ለማከናወን የሚችለው የኣገሬው ህዝብ በመሰረቱ የተለመደውን ታዛዥነትና አክብሮት ሲቸረው ነው፣ ህዝቡ ይህንን ታዛዥነትና አክብሮት በመሰረቱ ከነፈገው ግን መንግስት መቆምያ የለውም። ይህ እውነታ ለግለሰብም ለድርጅትም ይሰራል።

ይህ ስልት በአለም ኣቀፍ ግንኙነትም የሚሰራበት ስልት ነው፤ የተለያየ ክብደት ያላቸው ማእቀቦች በመጣል ይገለፃል፤ ማእቀቡ በግለሰብ ባለስልጣናት፣ በሃገሪቱ በጠቅላላ ወይም በተወሰኑ የሃገሪቱ ተቋማትና ድርጅቶች ላይ ሊጣል ይችላል። ሸማቾች እንደዚሁ በአንዳንድ በዳይ የንግድ ድርጅቶች ላይ ሲጥሉት ይታያል። በሃገራችን ባህላዊና ሃይማኖታዊ ማእቀቦች ይደረጋሉ፣ ቀሳውስትና ካህናት ይገዝታሉ፣ ማህበረሰብም ለህብረተሰቡ ህልውና እና ሰላም አደጋ ናቸው ያላቸውን ግለሰቦች የማግለል እርምጃዎች እንደሚወስድ ይታወቃል።

መንግስት እንግዶች ጋብዞ እና ደግሶ አንድ ታላቅ በአልና ፌስታ በሚያዘጋጅበት ወቅት በዚሁ ባለመሳተፍና ባለመገኘት በአሉ የተጠበቀውን ግርማ ሞገስ እንዲያጣ እና መንግስትም እንዲያፍር ማድረግ፤ በማንኛውም መልኩ ማንኛውም ሰው ከቤት ሳይወጣ ለተወሰኑ ቀናት እንዲቀመጥ ማድረግ፤ፌስቲቫል፣ ስፖርታዊ ተርኢት ወይ ሌላ ትልቅ በአል ተዘጋድቶ ህዝቡ እንዲመለከት በሚጋበዘበት ጊዜ ወደእሱ በመሄድ ፈንታ ወደ ቤተ ፀሎት መሄድ፤ ወይም የፖለቲካ እስረኞችን መጠየቅ፤ የተማሪዎች ትምህርት የማቆም እርምጃ፣ የመሳሰሉት እርምጃዎች ከማህበራዊ የአሻፈረኝ ስልቶች በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ከኢኮኖሚያዊ ያለመተባበር ስልቶች በጣም ከሚታወቁት ውስጥ አግልግሎትን ላለመጠቀም ወይም ላለመሸመት መወሰን፣ ክፍያን መክፈል ላይ መለገም፣ ስራን የማቆም ወይም የማስተጓጎል ስልቶች ናቸው። እያንዳንዱን ስልት በተለያዩ እርከኖች እና ደረጃዎች ተግባራዊ ማድረግም ይቻላል። ስራ ማቆም ለምሳሌ ብንወስድ በአንድ ተቋም ብቻ ወይም በኢንዱስትሪ ደረጃ ሊደረግ ይችላል፣ ስራ ማቆሙ ለቀናት የሚደረግ ወይም ከስራ ገበታ ሳይለዩ በድንገት በማሃል ላይ ለተወሰኑ ሰኣታት የሚደረግ ሊሆን ይችላል፣ ከማቆም ይልቅ ሆን ብሎ ስራን ማጓተትም ሊመረጥ ይቻላል፣ኣለቃና ተቆጣጣሪ ሲኖር መስራት፣ እርሱ ዞር ሲል ደግሞ በማቆም ያለተቆጣጣሪ ስራ መስራት የማይቻልበት ሁኔታ መፍጠር ይቻላል። የዚህ አይነት ስልት በተለይ ስራተኞችን ለመከፋፈልና ለመደለል አስቸጋሪ ያደርገዋል። ስራ ማቆምን ገልብጦ መተርጎም እንደ

የዚሁ ክፍል ስልት ሊወሰድ ይቻላል፡፡ ብዙ ሰው ስራ ገበታ ላይ በመገኘት እና ያለእረፍት በመስራት የተለመደውን የስራ ፍሰት ማፋለስ ይቻላል፡፡ አግልግሎትን እና ሸመታን ማወክ፤ተጠቃሚዎች ራሳቸው ባለመሸመትና ባለመጠቀም መልኩ ሊፈፅሙት ይችላሉ፣ አግልገሎቱን በሚሰጡ ሰራተኞች በኩልም ሊከናወን ይችላል ወይም ምርቱን በሚያከፋፍሉት፣ በሚያጓጉዙት፣ በሚጭኑት እና በሚያራግፉት በኩል፤ ወይም በሁሉም የተቀናጀ እርምጃ ሊፈፀም ይችላል፡፡

ከፖለቲካዊ ያለመተባበር ስልቶች ውስጥ በመራጭነት፣በተመራጭነት ወይም በሁለቱም ባለመሳተፍ፤ፓርላማ ስብሰባን ረግጦ በመውጣት፣ ኮረም እንዳይሞላ በማሰናከል ወይም ውሳኔ እንዲዘገይ በማደረግ፤ የፓርቲ ኣባልነት ካርድን በመመለስ፣ ሹመትን ባለመቀበል፤ ከተቀመጡበት ሃላፊነት በገዛ ፈቃድ መልቀቅ የመሳሰሉት በምሳሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

ትብብርን መንፈግና አሻፈረኝ የማለት ስልቶች ዋና አላማቸው ገሸሽ ካላችሁን እኛም ገሸሽ ማለት እንችላለን በዚሁም ለመቀጠል እና ለመኖር እንችላለን የሚል ግልጽ መልእክትና ተቃውሞ ማስተላለፍያ መንገድ ነው፣ ይበልጥ ውጤታማ የሚሆነውም ከሁለቱም አንዳቸውም ያለሌላው ትብብር እና በጎ ፈቃድ ብዙ ሊቀጥሉና ሊኖሩ የማይችሉ ሲሆኑ ነው፣የተፈለገውን ወጤት ለማግኘት ይቻል ዘንድ እርምጃው በሚያሳምም ወቅትና በከፍተኛ ተሳተፎ መታጀብ ይኖርበታል፡፡

### 5.1.3. የሰላማዊ ጣልቃገብነትና ተነሳሽነት ስልቶች

በዚህ ምድብ የሚጠቃለሉት ስልቶች ከላይኞቹ ሁለት ምድቦች ስልቶች የሚለዩት፤ ተቀናቃኙን ወገን የመጋፈጥ ባህርይ ያላቸው መሆኑ ነው፡፡ የሚወሰዱት እርምጃዎች በተቃዋሚው ወገን ተነሳሽነት የሚወሰዱ እና የተጀመሩ ሊሆኑ ይችላሉ ወይም ደግሞ ተቀናቃኙ ሊወስድ ያሰባቸውን እርምጃዎች ለማክሸፍና ለማኮላሸት ተብለው የሚወሰዱ የመከላከል እርምጃዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ እስርቤቶችን ማጥለቅለቅ የሚለውን ስልት ብንውስድ ህዝቡ ይህንን እርምጃ የሚወስደው እንደመከላከያ እርምጃ ሊሆን ይችላል፤ ወይም በህዝቡ ተነሳሽነት እንደሚወሰድ እርምጃ ሊሆን ይችላል፡፡  መንግስት የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችን ካሰረ እነሱ ይፈቱ ብሎ በመጠየቅ ፈንታ ህዝቡ እኛንም እሠሩ ብሎ ወደ እስር ቤቶች ሊጎርፍና እስር ቤቶችን ለያጥለቀልቅ ይችላል፤ ወይ ደግሞ የመንግስትን ፖሊሲዎች ከመቃወምና መታሰርን እንደአንድ የተቃውሞው መግለጫ በመውሰድ እስርቤቶችን በገዛ ራሱ ፈቃድ ሊሞላቸው ይችላል፡፡

የጣልቃ ግብነት ስልቶች የተለያየ ክብደትና ደረጃ አላቸው፡፡ አንድ በአድሎ የሚሰራን ባለስልጣን ለመቃወም ተበዳዮች ቢሮው ውስጥ ገብተው ካላነጋገርከን አንለቅም በለው ቁጭ ሊሉ ይችላሉ፡፡ ይህንን በማድረግም ሰውየው ሊያነጋገራቸው የሚፈልግን ሰዎች አስገብቶ እንዳያነጋግር፣ በሰኣት ስራውን እንዳይሰራ፣ ሲመሽ ከቢሮው ወጥቶ ወደ ቤቱ እንዳይሄድ፣ አስቸጋሪ ሁኔታ ሊፈጥሩበት ይችላሉ፡፡ አንድ ሆስፒታል ስራው በተገቢው መስራት አሻፈረኝ ካለ ታካሚዎች ተሰብስበው መጥተው ግቢውን እና ኮሪደሩን ሊተኙበትና ሊቀመጡበት ይችላሉ፣ የመንግስትን እርምጃ የሚቃወሙ ገበሬዎች ከብትና ኣጋሰስ እየነዱ በመምጣት የመኪና መንገዶችን ሊያጥለቀልቁ ይችላሉ፣ ከብት ከመንዳት ይልቅ ሰው መንገዶቹ ላይ ሊቀመጥ ወይም በመኪና መጓዝን ትቶ የመኪናውን መንገድ ወደ እግረኛ መንገድነት ሊቀይር ይችላል፡፡

በሰላማዊ መንገድ አንድን ተቋም ወሮ መያዝም ከጣልቃ ገብነት ስልቶች አንዱ ነው፡፡ አንድ በቅርቡ ለንደን ሂትሮ አውሮፕላን ማረፊያ ላይ የተፈፀመ የተቃውሞ

እርምጃ በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ አውሮፕላን ማረፊያውን የማስፋፋት በመንግስት የተያዘ እቅድ ኣለ፣ በሌላ በኩል ደግሞ አውሮፕላን ማረፍያው የሚፈጥረው የድምፅ ብክለት ያማረራቸው እና መስፋፋቱን የሚቃወሙ የአየር ንብረት ተንካባካቢ ወገኖች ኣሉ፡፡ አንድ ቀን ከነዚህ ተቃዋሚዎች የተወሰኑት የጥበቃና የፍተሻ ኬላዎችን በረቀቀ ጥበብ ኣልፈው ማኮብኮብያው ዘንድ በመድረስ አንድ ሊበር የተዘጋጀ አውሮፕላን ላይ ወጥተው መልእክታቸውን ከማስተላለፍ ባሻገር የሂትሮን ስራ ለተወሰነ ሰኣታት አስተጓጎሉ፡፡ የዚህ ኣይነት ጣልቃ ገብነት እርምጃዎች እንደየሃገሩ ሁኔታና እንደ አጀንዳው ባህርይ በተለያየ መልኩ ተግባራዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አግባብ ባልሆነ መንገድ መሬታቸው የተነጠቁ ዜጎች ሾልከው በመግባት መሬቱን ሊይዙና ድንኳን ሊተክሉበትና ባንዴራ ሊያወለበልቡበት ይችላሉ፡፡ ለእንድ ትልቅ በኣል፣ለምሳሌ ስፐርታዊ ወይም ሙዚቃዊ ፌስቲቫል፣ የተጠሩ በኣስር ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ጉዳዩ ካለቀ በኋላ ቦታውን በመልቀቅ ፈንታ ቢቀመጡበትና ስሞታቸውን መግለጫ ቢያደርጉት ከዚሁ ምድብ ስልት ይሆናል፡፡

ጣልቃ ገብ ስልቶች ሰላማዊ በሆነ መንገድ የሚከናወኑ ቢሆኑም ቅጣት አያመጡም ማለት አይደለም፤ ማታፈስ፣ መቀጣትን እና መደብደብን ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ ተሳታፊዎች የሃይል እርምጃ እንዳይወስዱ፣ ቢወሰድባቸውም አፀፋ ከመመለስ መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል፤ ይህን አልፎ የሚመጣባቸውን ጉልበት ግን በጋራና በፅናት ለመቀበል ዝግጁ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ከላይ እንደተመለከተው ሊያስሩት የመጡትን እንካችሁ እጄ ብሎ ወዶ የሚታሰር፣ ራሱ እስር ቤት ድረስ ሄዶ እስርቤቶችን የሚያጥለቀልቅ የሰላም ታጋይ ካለ የሃይል እርምጃው ተመልሶ የሚጎዳው ተበዳዮቹን ሳይሆን አድራጊዎቹን ራሳቸውን ነው፡፡ እስርና መቀጮ የመሳሰሉት እርምጃዎች ገዢዎች የሚጠቀሙባቸው እንደማስፈራርያ- deterent - ነው፡፡ ህዝቡ አንዴ ፍርሃትን ማሸነፍ እሚችልበት ደረጃ ላይ ከደረሰ ግን ሚልዮኖችን ማሰር የሚችል ፖሊስና እስርቤት ሚልዮኖችን ሊፈርድ የሚችል ችሎት ማግኘት ሰለማይቻል፤ የማታ ማታ ተሸናፊ የሚሆነው ጉልበተኛ ነኝ ባዩ መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡

## 5.2. የስልቶቹ አጠቃቀም መርሆዎች

### 5.2.1. አይመቼነት

ኣይመቼነት- asymmetricity - አንድ ተፋላሚ ሃይል ተቀናቃኙን ለእሱ በሚመቸው እና በሚያዋጣው መንገድ እንጂ ለተቃናቃኙ በሚመች መንገድ ሊገጥመው ኣይገባም የሚለውን መርህ ለመግለፅ የመጣ አባባል ነው፡፡ ተቀናቃኝህን እርሱ በተዘጋጀበት እና በሚያውቅበት መንገድና ዘዴ ከመጣህበት ወዮልህ፤ እርሱ የተዘጋጀበትን እና የሚያውቅበትን መንገድ እና ዘዴን ትተህ በሌላ በማያውቅበት መንገድና ዘዴ ከመጣህበት ግን የማሸነፍ እድል ይኖርሃል፤ ይላል የኣይመቼነት መርህ፡፡ ይህ መርህ ትጥቅ ትግልንንና ሰላማዊ ትግልን ጨምሮ ለማንኛውም ፍልሚያ የሚሰራ መርህ ነው፡፡

የገናናው የጦር መሪ ናፖሌዎን ቦናፓርቴ ሰራዊት የመላ አውሮፓ ነገስታት ሰራዊትን እንዳላርበተበተ ሁሉ ኋላ ላይ ጉድ የሆነው ሰፔይን ውስጥ በተቀሰቀሰበት ሽምቅ ውጊያ ነበር፡፡ ይህ ሊሆን የቻለው የስፔይን የነፃነት አርበኞች ይዘውት የመጡት የጦር ስልትና አደረጃጀት የናፖሌዎን ሰራዊት ከሚያውቅበትና ከተደራጀበት ፈፅሞ የማይጣጣም በመሆኑ፣ ለናፖሌዎን ጦር ጠንካራ ምትና ክርን አሳርፎ ጦርነቱን ባንዴ ለመጨረስ የማይቻል ስላደረገበት ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ሽምቅ ውጊያው የኣጥፍቶ

መጥፋት ስልትም ተጨምሮበት እጅግ ዘመናዊ መሳሪያ፣የመገናኛና የመረጃ ቴክኖሎጂ የያዘ ከሰባ ሺ በላይ የኔቶ ጦር በተሰለፈበቱ የአፍጋኒስታን ጦርነትም አስቸጋሪ ሁኔታ ፈጥሮ ይገኛል፡፡

በሰላማዊ ትግልም ይህንን መርህ አጥብቆ መከተል እጅግ ኣስፈላጊ ነው፡፡ አፋኝ መንግስታት የመጀመርያው ምርጫቸው ህዝቡ ከሩቁ በፍርሃት መታገሉንና መቃወሙን ባይከጅለውና አርፎ ቢገዛላቸው ነው፡፡ ይህ እውን ይሆን ዘንድ የድለላ ስልቶችን ከማስፈራራት ስልቶች ጋር በማፈራረቅ የህዝቡን ትግል ለማኮላሸት አበርትተው ይሰራሉ፡፡ በሂደት ህዝቡ እነዚህን እየተሻገራቸው ሲሄድ፣ ንቃቱና አደረጃጀቱ እያደገ፣ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች እየከበዱ መሄዳቸውን ሲገነዘቡ ተቃዋሚዎቹ የስልት ስህተት ፈፅመው በእነርሱ መንገድ ለእነርሱ በሚመቸው ስልት እንዲመጡላቸው ኣጋጣሚውን ይጠብቃሉ፤ ያ ኣጋጣሚ ይመጣላቸው ዘንድም ሆን ብለው ሊሸርቡ ይችላሉ፡፡ ያ አምባገነኖች የሚቋሙጡለት ስልት ደግሞ የአመፅና የሃይል ስልት ነው፡፡ መንግስት የተደራጁና በሚገባ የታጠቁ የመከላከያ እና የፀጥታ ሃይሎች በእጁ በያዘበት ሁኔታ ላይ ይህንን መንገድ መከተል ደግሞ ውጤቱ ጥፋት ከመሆን አይዘልም፡፡ በዚህ ፈንታ ሃይሉን ለመጠቀም የማያስችሉትን፤ ቢጠቀምም እንኳ ውጤት የማያስገኙለትን የሰላማዊ ትግል ስልቶችን እየመረጡ መጠቀም ነው የሚገባው፡፡

### 5.2.2. ስትራተጂ መር

ስለ ሰላማዊ የትግል ስልቶች እና አጠቃቀማቸው ጠለቅ ያለ እውቀት መያዝ በዚሁም ዙርያ ጥናትና ምርምር ማካሄድ እጅግ አስፈላጊ ነው፣ ይህ ስለተያዘ ግን ዘሎ ወደ ትግበራቸው ይኬዳል ማለት አይደለም. የእያንዳንዱ ሃገር ሁኔታ ከሌላው ሃገር ሁኔታ የሚያመሳስል እንዳለው ሁሉ የሚለይባቸው ሁኔታዎችም እንዳሉ፣ በእያንዳንዱ ሃገር ለሚካሄደው ትግል እነዚህ ልዩ ሁኔታዎች ትልቅ ኣሻራ እንደሚያሳርፉ በቂ ግንዛቤ ሊያገኝ የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

ከፍ ብሎም እንደተመለከተው ስልቶች በፖለቲካ ፕሮግራምና በኣጠቃላይ የትግሉ ስትራተጂ መመሪታቸው የሚመረጡት ስልቶች እና አጠቃቀማቸው ከተጨባጭ የሃገሪቱ ሁኔታ ጋር እንዲቆራኙ ያደርጋል፡፡ ይህ ሲሆን ስህተቶች እንዳይፈፀሙ፣ ቢፈፀሙ እንኳን ጉዳታቸው እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡. ከሁሉም በላይ ደግሞ የልፋቱ እና የመስዋእቱ የፍሰት ኣቅጣጫ ወደ ድል አቅጣጫ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

### 5.2.3. አዳጊነትና ተደማሪነት

በሰላማዊ ትግል ዋና ተዋናዩ ምልአተ-ህዝቡ እንደመሆኑ መጠን ከስልቶቹ ጋራ ተዋውቆ በብቃት ተግባራዊ የሚያደርግበት ደረጃ ላይ እስከሚደርስ በቂ የመለማመጃ ትግልና ጊዜ ያስፈልገዋል፣ በዚሁ ወጥተን በዚሁ ገብተን እንደዚህ እናደርጋለን ተብሎ እቅድ ስለወጣ ብቻ እንዲሁ ነገሩ ከመጀመርያው ቀን ጀምሮ በተሳካ ይሄዳል ማለት አይደለም፡፡ሰላማዊ ትግልም የራሱ በዲሲፕሊን የታነፀ አዋጊና ተዋጊ እንደሚያስፈልገው መረሳት የለበትም፡፡

የስልቶቹ አመራረጥ ከህዝቡ የትግል ግንዛቤና ልምድ ጋራ ማደግ ይኖርበታል፡፡ በቂ ድጋፍ እንዳለው ሳያረጋግጡ ወደ የጣልቃገብነት ስልቶች መግባት የተፈለገውን ውጤት ላያስገኝ ይችላል፡፡ ከዚህ ይበልጥ መጀመርያ ስራ ላይ መዋል ያለባቸው ስልቶች የመጀመርያ ምድብ ስልቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ይህ ሲባል ልምዱና ብቃቱ ከተግባር ብቻ የሚገኝ መሆኑን ሳይሳት ነው፡፡ ብቃቱ እና ልምዱ የሚጠራቀመው ከየእለቱ መለስተኛ ልምዶች እንደመሆኑ መጠን የተገኘውን

ሃይል ይዞ ካልተገኘም ብቻ ሆኖ ሁሌ መጮህ እና አይበገሬነትን ማሳየት ያስፈልጋል፡፡ አንዴ ገባ፣ ሲሞቅ ደግሞ ወጣ እያሉ የሚደረግ ትግል ተደማሪ እና አዳጊ ሆኖ ለቁም ነገር አይደርስም፡፡

### 5.2.4. ተያያዥነት

ሰላማዊ የትግል ስልቶች ይህን ያክል ናቸው፣ በሶስት ዋና ዋና ምድቦች ይመደባሉ መባሉ፣ ለግንዛቤ እንዲመች ተብሎ እንጂ እንዳው ስልቶቹ ይህን ያክል የተራራቁ ሆነው አይደለም፡፡ የአለመተባበር እና ኣሻፈረን የማለት ስልቶች በተወሰነ ደረጃ የጣልቃገብነት ስልቶች ባህርይ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ልዩነቱ ያለው ዋናው ባህርያቸው የቱ ጋር ነው? ያለው ነው፡፡ ከአለመተባበር ወደ ጣልቃገብ ስልቶች ሲሸጋገሩም እንዲሁ አንደኛው ከየት ኣቆመ? ተከታዩ ከየት ጀመረ? የሚለውን መለያ መስመር ማስቀመጥ አይቻል ይሆናል:: ሽግግር መፈፀሙን ግን ከአጠቃላይ ፍሰቱ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ከቤት ያለመውጣት ካለመተባበር ምድብ ይመደባል ሲባል የጣልቃገብነት ገፅታ የለውም ማለት አይደለም፡፡ ነጋዴው ሱቁን ዘግቶ፣ ሹፌሩ መኪናውን አቁሞ፣ የፋብሪካ ሰራተኛውም ፋብሪካውን ዘግቶ፣ ቤቱ ሲቀመጥና ሁሉም ቀጥ ሲል የለየለት ሁለገብ ጣልቃገብነት ይሆናል፡፡

በኣንድ አገር ተሆኖም በአንዱ ጫፍ ያለው ህዝብ ሌላው ጫፍ ካለው ህዝብ ጋር ያለው የትግል እድገት አንድ ሊሆን ስለማይችል የትኛው ስልት የትኛው አካባቢ ላይ ይሰራል? ለሚለው መልሱ ይለያያል፡፡ እንደየአካባቢው ሁኔታ ስልቶች ሊለያዩ እንደሚችሉ ተገንዝቦ ሁሉም ሊሸከመው በሚችል ደረጃ አስልፎ ትግሉን እንዲቀላቀል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### 5.2.5. ህዝባዊነት/አሳታፊነት

ዴሞክራስያዊ ለውጥን ማምጣት ይሁን የተገኙትን ዴሞክራስያዊ ድሎች እና እሴቶችን መጠበቅና መከላከል የምልአተ ህዝቡ ፋንታ ነው፡፡ የፓርቲዎች ሚና ህዝቡ ይህንን ያሳካ ዘንድ በጥናት የተመሰረተ ስትራተጂ ማዘጋጀትና በህዝቡ መሃል ሆኖ ይህን ስትራተጂ ያሳካው ዘንድ ማስተባበር ነው፡፡የተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ብቻ በሚያደርጉት "ቆራጥ" ተጋድሎ ዘለቄታዊ ፋይዳ ያለው ዴሞክራሲ ሊመጣ እንደማይችል፣ ከመጣም እነዛ ታግለን አመጣን ያሉት ወገኖች ያንን አመጣን ያሉትን ዴሞክራሲ መልሰው ሊወስዱት እንደሚችሉ ያለፈው የሰላሳና አርባ አመታት የኢትዮጵያ ታሪክ አሳይቶኣል፡፡

ይህ እንዳይደገም ህዝቡ በትግሉ በሚልዮኖች በቀጥታ እንዲሳተፍ የሚያደርግ አካሄድ መከተል እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ በየጊዜው በምትደረገዋ ትግል የሚሳተፍ ሰው በየጊዜው የፍርሃት መከላከያ ክትባት እንደወሰደ ነው የሚቆጠረው፤ መከላከያ ክትባቱ ብዙ ህዝብ ጋር እንዲዳረስ ማድረግ ብዙ ሰዎችን በፍርሃት ልክፍት እንዳይጠቁ ማስቻል ማለት ነው፡፡

ሰላማዊ ትግል በባህሪው ሽማግሌው፤ ወጣቱ፤የአካል ጉዳተኛው፤አርቲስቱ፤ ሳይንቲስቱ፤አትሌቱ፤ሹፌሩ፤ሜካኒኩ ወዘተ ፆታ፤ቀለም፤ቋንቋና ሃይማኖት ሳይለይ ያለ ብዙ መፈናቀል ሁሉን ሊያሳትፍ የሚችል የትግል መልክ ነው፡፡ አሳታፊና ህዝባዊ ይሁን ሲባል ይህን ባህሪው ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ ማዋል ማለት ነው፡፡

## 6. የሰላማዊ የትግል ስልቶች ተገባራዊነት በኢትዮጵያ

በንጉሱ ዘመን ይሁን በደርግ ዘመን ሃሳብን በነፃ የመግለፅ፣ ሰላማዊ በሆነ እና በተደራጀ መልኩ መንግስትንና ፖሊሲዎቹን መቃወም ወይም ህዝቡ ያልፈለገውን መንግስት በነፃ ምርጫ ማስወገድ የሚባሉት ዴሞክራስያዊ መብቶች የሚታሰቡ አልነበሩም፡፡ በመሆኑም በወቅቱ እነዚህን መብቶች መጠቀም ለእስር ለድብደባ ለቅጣትና ለሞት ሊዳርግ የሚችል ህገወጥ ድርጊት ነበር፡፡

በእነዚህ መብቶች መጠቀም ህገወጥ ነው ተብሎ ቅጣት ቢደነገግበትም ህዝቡ በእነዚህ መብቶች ከመጠቀም ሙሉ በሙሉ ታቅቦ ነበር ማለት አይደለም፡፡ በንጉሱ ዘመን እነዚህ ከልካይ ድንጋጌዎች የኣሳሪነት ሚና ቢታይባቸውም ህዝቡ በሂደት ፍርሃቱን እያሸነፈ እና ተግባሩ የሚያስቀጣ መሆኑን እያወቀም ተቃውሞውን በግልፅ ወደ አደባባይ ማውጣት ችሎኣል፡፡ በስድሳዎቹ አጋማሽ የታየው መላ ኢትዮጵያውያን የተሳተፉበት ህዝባዊ እንቅስቃሴ የዚህ በሂደት እየተጠራቀመ የመጣውን ፍርሃትን የማሸነፍ ትግል ውጤት ነው፡፡

ደርግ ስልጣን የያዘ እለት አፍ መፍቻ ያደረገው አዋጅ መሰብሰብንና መቃወምን የሚከለክል የሆነበት ምክንያት የንጉሱ ደጋፊዎች ተነሳስተው እንዳይጥሉት ከመስጋት ሳይሆን ያ የንጉሱን ዘውዳዊ አገዛዝ ያናጋው የህዝብ ትግል ራሱን ደርግንም ጠራርጎ ገደል እንዳይከተው ስለሰጋ ነበር፡፡ ይህንን ደንግጎም ለዴሞክራሲ የሚደረገውን ትግል ሊገታው የማይችል መሆኑን ሲገነዘብ ነበር ወደ ቀይሽብር እርምጃ የገባው፡፡ በቀይ ሽብር ዘግናኝ እርምጃዎች ምክንያት በህዝቡ ስነልቦና የተፈጠረው የፍርሃት ድባብ በሃገሪቱ ውስጥ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ሰላማዊ ትግል ተዳክሞ እንዲቆይ ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

የደርግ መንግስት ተወግዶ የሽግግር መንግስቱ የተመሰረተበት ቻርተር ይፋ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ እነዚህ መብቶች ህጋዊ እውቅና አግኝተዋል፡፡ ቻርተሩን ተክቶ ስራ ላይ ባለው የኢፌድሪ ህገ-መንግስት ጋር ሲመጣም ምእራፍ ሶስት ስር በተዘረዘሩት አንቀፆች አማካኝነት ሁሉም መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች የተከበሩ መሆናቸው ተደንግጎአል፡፡ ከዚህ አለፍ ተብሎም በዚህ ምእራፍ የተዘረዘሩት የመሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ድንጋጌዎች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው አለምአቀፍ የሰብአዊ መብቶች ህግጋት፣ አለምአቀፍ የሰበአዊ መብቶች ስምምነቶችና አለምአቀፍ ሰነዶች መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ እንደሚተረጎሙ (አንቀፅ13/2)፣ ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው አለምአቀፍ ስምምነቶች የሃገሪቱ ህግ አካል እንደሆኑ (አንቀፅ9/4)፣ በህገ-መንግስቱ ተደንግጎአል፡፡ በእኛ ኢትዮጵያውያን መሃከል በአንቀፅ 39 ዙርያ ልዩነት ቢኖርም መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች የህጎች ሁሉ የበላይ በሆነው ህገ-መንግስት ውስጥ ይህን ያክል ስፍራ መያዛቸው አንድ ታላቅ እርምጃ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡

ኢህአዴግ ለእነዚህ መብቶች እና ነፃነቶች ድጋፍ ነበረው፣ በዚህ ምክንያትም ነው በህገ-መንግስቱ ሊሰፍሩ የቻሉት፡፡ በህገ-መንግስቱ ይህንን ቢቀበልም ከዚህ ጋር የማይሄዱ ሆኖም ግን ፓርቲው የያዛቸው አቋሞችና እምነቶች በመኖራቸውና አነዚህንም ሳያስተካክል በመሄዱ ውሎ አድሮ በህገ-መንግስቱ እና በፓርቲው አቋም መሃከል ተቃርኖ መፈጠሩ አይቀሬ ነበር፡፡ በሂደት ግልፅ እየሆነ የመጣው እውነታ የሚያሳየውም ይህንኑ ነው፡፡

በአንድ ህብረተሰብ ዴሞክራሲ አለ ለማለት የሚቻለው አንደኛ በግለሰቦች እና ፓርቲዎች ማሃከል ነፃ የሃሳብና የአቋም ውድድር ኖሮ የተሻለ ሆኖ የተገኘው ወገን ለስልጣን የሚበቃበት ከጉልበት የፀዳ ስርኣት ሲኖር ነው፣ ሁለተኛ ዜጎች ያላንዳች

ገደብና መሸማቀቅ ምርጫቸውን ለመግለፅ የሚችሉበት እጅግ አሳታፊ የሆነ የምርጫ ስርኣት ሲዘረጋ፣ ሶስተኛ በፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም በሌላ መልኩ ተደራጅቶ ያመኑበትን ሃሳብ ለማራመድ የደገፉትን ለመምረጥና ሃሳብን ያለፍርሃት ለመግለፅ የሚያስችል መሰረታዊ መብቶችና ነጻነቶች የተረጋጋጡበተና የተከበሩበት ፖለቲካዊ ምህዳር ሲኖር ነው። ለአንድ ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ህልውና የእነዚህ እሴቶች በጋራ ተሟልቶ መገኘትን ግድ ይላል(1)።

የኢፌድሪ ህግ-መንግስት ሶስቱንም ሲቀበል የኢህኣዴግ አብዮታዊ ድሞክራሲ መስመር ግን የአንድን ፓርቲ የበላይነት ለማስቀጠል የቆመ በመሆኑ ፖለቲካዊ ምህዳሩን ለአንድ ፓርቲ ኣገዛዝ በሚመች መልኩ እንዲቀይስ ግድ ስለሚል ህገ-መንግስቱን ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ በተጣጣመ መልኩ ብቻ እንዲያየው እና በዚሁም ከኢፌድሪ ህግ-መንግስት ጋር እንዲጋጭ ግድ ሆኖበታል።

ይህንን እውነታ ለማሳየት ሩቅ መሄድ አያስፈልገንም። ኢህኣዴግ የፓርቲዎችን የፋይናንስ ምንጭ እንዲደርቅ የሚያደርግ፣ የግብረሰናይ/ሲቪክ ድርጅቶችን የገንዘብ ምንጭ እንዲደርቅ የሚያደርግ፣ የግል ፕሬስ በአስፈሪ ቅጣት ምክንያት አንደበቱ እንደሸበብ የሚያደርግ፤ ኣዋጆችን በማወጣት ተጠምዶ ያለው አማራጭ ሃይል፣ አማራጭ ድምፅ እንዳይመጣበት አስቀድሞ ለመዝጋት ለመሆኑና እነዚህ አዋጆች በህገ-መንግስቱ ከሰፈሩት መብቶች እና ነፃነቶች ጋር የሚጣረሱ ስለመሆናቸው ከኢህአዴግ በስተቀር የሚጠራጠር ወገን የለም። የእህል ውሃ ጉዳይ ሆኖባቸው ካልሆነ በቀር የእነሱም ልቦና ቢሆን ይህን እውነታ ይስተዋል ብሎ መገመት ያስቸግራል።

ኢህአዴግ ደርግን ለማሸነፍ ያስቻለው ወታደራዊ ቀመር (ወታደራዊ ዶክትሪን/ መስመር)ነበረው፣ ይህ ቀመር ደርግን ከማሸነፍ አኳያ ወሳኙ ስልት የተራዘመ የትጥቅ ትግል መሆኑን አስቀመጦ ከዚሁ በተጨማሪ እና በደጋፊነት ደግሞ የከተማና የገጠር የህዝብ አመፅን፣ ህጋዊና ህጋዊ ያልሆነ ሰላማዊ ትግልን መጠቀምንና እነዚህን ሁሉ ያጣመረ ሁሉን አቀፍ ትግል ማካሄድን የተቀበለ ነበር። በአሁኑ ወቅት ኢህአዴግ ደርግን ጥሎ ስልጣን ላይ ያለው እርሱ መሆኑ ቢታወቅም ይህ ቀመር ግን አሁንም ድረስ ከድርጅቱ አስተሳሰብ የተፋቀ አይመስልም። ተቃዋሚዎች ከፈለጉ ኢህአዴግ ባስቀመጠላቸው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የዴሞክራሲ ትርጉም ይሄዳሉ፤ ይህን ትተው ህገ-መንግስቱ በደነገገው መንገድ ከሄዱና የፓርቲውን ስልጣን ካነቃነቁ ግን የሚጠብቃቸው ጉልበት መሆኑ ኢህአዴግ አሳይቷል። በዚህ ፅሁፍ አቅራቢ እምነት ምርጫ 97 ላይ ለተፈጠረው ሁኔታ የተቃዋሚዎቹ ጉድለት የራሱ አስተዋፅኦ ቢኖረውም ሃላፊነቱ በዋናነት የሚወድቀው በገዢው ፓርቲ ላይ ነው::

ገዢው ፓርቲ ሲበርድ በሰላማዊ መንገድ ሲሞቅ ደግሞ በጉልበት እያለና ከሁለቱም እንዳስፈላጊነቱ እያጣቀሰ መጠቀም ቢመርጥም፤ የዚህ ፅሁፍ ኣቅራቢ "ኢህዴግን ማሸነፍ የሚቻለው በዚያ እርሱ በመጣበት የጥይት ቋንቋ ነው " ከሚሉት ወገኖች ጋርም አይስማማም፣ ኢህኣዴግን እርሱ በመጣበትና በሚያውቅበት መንገድ መፋለም ጨዋታውን ለእርሱ የበለጠ አመቺ ያደርገዋል ወደ ዴሞክራሲ መዳረሻነቱም ኣጠራጣሪ ነው ብሎ ያምናልና።

ሰላማዊ የትግል መንገድ በአሁኑ ዘመን ይቅርና በንጉሱ ዘመንም የማይናቅ አስተዋፅኦ አድርጓል፣ ህጋዊ እውቅና ካገኘ ወዲህም ህዝቡ በተለያየ መልኩ ሲለማመድበት ቆይቷል፣ ምርጫ 97 ላይ በተለይ በተለያየ መልኩ በስፋት በተግባር ላይ

..........................

1. George Sorensen, Democracy and Democratizaion P.13

ውሎአል፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ከዚህ ያገኘው ጥልቅና ሰፊ ልምድና ትምህርት እንዳለ ለአንድአፍታ እንኳ ሊዘነጋ አይገባም።

ኢህኣዴግ የሚፈጥረው ችግር እያለም በሰላማዊ ትግል ለድል ለመብቃት ይቻላል። እስካሁን በተደረገው ትግል ውጤት ለማግኘት ያልተቻለው በተቃውሞው ሰፈር ላይ አሁንም ድረስ ያልተፈቱ ሁለት መሰረታዊ ችግሮች ስላሉ ነው። አንደኛው የህብረት ጥያቄ ተግዳረቱ በሚጠይቀው ደረጃ መልስ ያለማገኘቱ ሲሆን ሁለተኛውም ከዚህ የተያያዘ ግን ራሱን ችሎ መመለስ ያለበት የአገርአቀፍ ስትራተጂ ያለመኖር ጉዳይ ናቸው። ለተቃዋሚዎቹ ለራሳቸውም ለአገርም የሚበጀው ለእነዚህ ችግሮች መፍትሄ መስጠት ነው።

ለማጠቃለል በሰላማዊ መንገድ ለዴሞክራሲያዊ ለውጥ የሚደረገው ትግል የሚያስፈራው ኢህኣዴግን ራሱን እንደሆነ በግልፅ እየታየ ያለበት ወቅት ላይ ነው ያለነው፣ ይህም ሆኖ ተቃዋሚዎች ማድረግ ያለባቸው ህገ-መንግስቱን በማክበር ኢህኣዴግን መታግል እንጂ ለእርሱ ወደሚመቸው የሃይል መንገድ መግባት መሆን የለበትም። ካለፈው የሰላማዊ ትግል በጎ ልምዶችና ስህተቶች የሚገባውን ልምድ መውሰድ ከተቻለ፣ ህገ-መንግስቱ እውቅና የሰጣቸውን መብቶች ጥበብ በተሞላበት መልኩ መጠቀም ከተቻለ፣ እና መላውን የኢትዮጵያ ህዝብ ሊያስተባብር የሚችል ህብረትና ወጥ ስትራተጂ ይዞ መውጣት ከተቻለ፣ በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ገጽ-ምድር ላይ ለውጥ ማምጣት ይቻላል። ህግ አክባሪ መሆን ፈሪ መሆን አይደለም፤ ሰላማዊ ትግል የፈሪዎች የትጥቅ ትግል ግን የደፋሮች አድርገው የሚያዩ ካሉ ተሳስተዋል። የገዛ ራሱን ፍርሃት ያላሸነፈ መንግስትን ለማሸነፍ ከቶ አይቻለውም።የገዛ ራሱን ፍርሃት ያላሸነፈ ደግሞ ለማንኛውም ፖለቲካዊ ትግል - የትጥቅ ይሁን ሰላማዊ - አይሆንም።